# ሴቶች በእስልምና እና የተለመዱ ስሁት ሃሳቦችን ማስተካከያ

ይህ መፅሐፍ የሚከተሉትን ጥያቄዎችን እና ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡

- በዘመናት ውስጥ- ሴቶች ከእስልምና በፊት ባለው የዐረብ ህብረተሰብ፣ የህንድ ህብረተሰብ፣ የቻይና ህብረተሰብ፣ የግሪክ ህብረተሰብ፣ የሮማውያን ህብረተሰብ፣ በባህላዊ የአይሁድ ህብረተሰብ፣ በባህላዊ የክርስትያን ህብረተሰብ እና በዘመናዊው ዓለማዊ ህብረተሰብ ውስጥ- የሴቶች አመለካከትና ይዞታ ላይ፣
- በእስልምና ውስጥ ሴቶች እና ወንዶች እኩል በሆኑባቸው ጉዳዮች ላይ፡- በመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች ላይ፣ ሃላፊነቶችን በመወጣት ላይ፣ በዚህችም ሆነ በመጪው ዓለም ለመልካም ሃሳቦቻቸውና ሥራዎቻቸው በሚያገኙት ሽልማት እና በተቃራኒው ለክፋቱ ደግሞ በሚደርስባቸው ቅጣት ላይ፣ በንብረት ባለቤትነትና የግብይት ልውውጥ ላይ፣ ክብርን፣ ማዕረግንና ጨዋነትን በመጠበቅ ላይ፣ በግዴታ ትምህርት ላይ እና ህብረተሰቡን በጎ ጎዳናን በማሳየትና በመምራት ረገድ ባላቸው ሃላፊነት ላይ፣
- በሙስሊሙ ህብረተሰብ ውስጥ በተለያዩ ዕድሜዎቻቸው እና ላይ የሴቶች ደረጃና መብት ላይ- በህፃንነት፣ በልጅነት እና ኮረዳነት ዕድሜዎቻቸው ላይ- እና በእህትነታቸው፣

በሚስትነታቸው፣ በእናትነታቸው፤ እንዲሁም ዘመድም ሆነ ጎረቤት ሲሆኑ እና በሴትነት በጥቅሉ ላይ፣

- ሴቶች በእስልምና ውስጥ ባላቸው መብቶችና ግዴታዎች ላይ በሚሰነዘሩ ስሁት ዕይታዎችና ማስተካከያቸው ላይ፡፡

## መቅድም

ምስጋና ሁሉ ለልቁ አላህ የተገባ ነው፡፡ አላህ በመልእክተኛው እና ቤተሰቦቻቸው ሥም መነሳት ላይ ልቅ ያድርጋቸው፤ ካልተገባ ነገር ሁሉ ይጠብቃቸው፡፡

ሴቶች በእስልምና ውስጥ ስላላቸው መብቶችና ቦታ አዲስ ነገር ልናገር (ላቀርብ) እንደማልችል አምናለሁ፡፡ ስለዚህ በዚህ ርዕስ ጉዳይ የተወሰኑ አስፈላጊ ናቸው ብዬ ያመንኩባቸው መረጃዎች ሰብስቤ ፣ አስተካክዬና ጨምቄ ለአንባብያን ለማቅረብ ሞክሬያለሁ፡፡ ዓላማዎቼን እንዳሳካ የአላህን (ሱ.ወ) ምሪት ተስፋ አደርጋለሁ፤ እፀልያለሁም፡፡

እስልምናን በሴቶች በደልና ጭቆና መክሰስ ስህተት ነው፡፡ በተለይ ክሶቹንና ውንጀላዎቹን በቀጥታ የሚያስተባብሉ በርካታ ንግግሮችን በቅዱስ ቁርአንና በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ትውፊቶች ውስጥ መኖራቸው ክሶቹ ሚዛናቸውን የሳቱ ያደርጋቸዋል፡፡

“እላንተ ሰዎች ሆይ እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤ አላህ ግልጽን ዐዋቂ፣ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።” (49፡ 13)

እንዲሁም በተጨማሪ አላህ (ሱ.ወ) ሲናገር

“ለናንተም፣ ከነፍሶቻችሁ (ከጐሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ፡፡” (30፡21)

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ

“በእርግጥ ሴቶች የወንዶች መንትያ ግማሽ ናቸው” ብለዋል፡፡ (አቡ ዳውድ 234 እና ቲርሚዚ 113 እና ሌሎችም)

## መግቢያ

ስለሴቶች ነፃነት፣ እንዳሻ መሆን እና የእኩልነት መብቶች በርካታ ድምፆች በዓለም ዙሪያ እየተሰሙ ናቸው፡፡ ለዚሁ ዓላማ በተካሄዱ ሰልፎች ላይ ብዙ መፈክሮች ተደምጠዋል፡፡ በተወሰኑ ህብረተሰቦች ውስጥ ሴቶች በጭቆና፣ ጭካኔና ኢፍትሃዊነት ውስጥ እየኖሩ ሲሆን መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶችን እንዳያገኙ ተከልክለዋል፡፡ የተወሰኑ ሙስሊሞችም ከእስልምና መርሆችና አስተምህሮዎች በማፈንገጥ የእነዚህ ህብረተሰቦች አካል ሆነዋል፡፡ እስላማዊው ህግ ግን የሴቶችን መብቶች በሰብአዊ መብቶችና እና ግዴታዎች ስርዓት ውስጥ ሚዛን ጠብቆ ሰብስቧል፡፡ በዓለም አቀፉ የሴቶች ነጻነት ቅስቃሴ መድረኮች የቀረቡ መፈክሮች በአትኩሮት ሲመረመሩ በሶስት ጭብጦች- 1) በሴቶች ነፃነት፣ 2) ከወንዶች ጋር እኩል መብት ይረጋገጥል እና 3) በሴቶች መብቶች- ዙሪያ ይሽከረከራሉ፡፡ ሶስቱንም በእስላማዊ ህግና አስተምህሮዎች እንመረምራቸዋለን፤ ከሃይማኖቱ ህግና አስተምህሮዎች ያፈነገጡትን ሙስሊሞች ሳንዘነጋ፡፡

በመጀመሪያ ነፃነት የሚለው ሃሳብ ቀንበር፣ እስር እና መገደብን እንደ ቅድመ ሃሳብ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም፣ በሁለተኛነት፣ በባርነት ውስጥ ያሉ ሴቶች ከባርነት አርነት መውጣት አለባቸው፡፡ ነገር ግን ይህ አሻሚና አሳሳች ነው፡፡ ምክንያቱም ወንድ ተሆነ ሴት ፍጹም ነጻነትን ሊያረጋግጡ አይችሉም፡፡ የሰው

ልጅ አብረውት በሚኖራቸው ውስን ችሎታዎቹ/ አቅሞቹ እና በማህበራዊ እቅባቶች ውስጥ የተገደበ ነው፡፡ ሁለቱም ፆታዎች የህይወትን የተለያዩ ጉዳዮች በሚያሳልጡና በሚያዋቅሩ የተወሰኑ ህግጋት፣ ደንቦች እና ቁጥጥሮች በፀኑባቸው ከባቢ ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ ይህ ግን ሰው ነፃነት የሌለው፣ እንቅስቃሴዎቹ የእርሱ ያልሆኑ፣ ለሚሠራው ሥራ በምንም አይነት ሃላፊነት አይጠየቅም ማለት ነውን? ከተፈጥሮ ወሰኖችና ህጋዊ ማዕቀቦች ነፃ ሊሆን የሚችል አለን? ሰዎች ባሪዎች ከሆኑ ተከታዩ ጥያቄ "ለማን?" የሚለው ይሆናል፡፡

የትኛውም ነፃነት እና እንዳሻ መሆን ተፈጥሮዋዊና ህጋዊ ወሰኖች አብሮት አሉ፡፡ የእነዚህ ወሰኖች መጣስ ውጤታቸው ዋልጌነት፣ አውሬነትና ወንጀለኝነት ወደ ሆኑ አጥፊ ተግባራት ያሻግራል፡፡ እስላማዊው ህግ ሁለቱም- ወንዶችም ሆኑ ሴቶች- ከጣዖት አምልኮ፣ ዕብሪት፣ ብዝበዛ እና ኢፍትሃዊነት አርነት እንዲወጡ ያውጃል፡፡ መለኮታዊ መርሆዎቹና ህግጋቱ ጥብቅ አንድ አምላክ አምልኮን፣ ፍትህንና ክቡር ሞራሊቲን (የስነ ምግባር መሠረቶችን) ያስተምራሉ፤ ያቀነቅናሉ፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ወንድና ሴት ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ ሚና አላቸው፡፡ እስላማዊው ህግ ሴቷ በህብረተሰብ ውስጥ በቀጥታ ተሳትፎ የማድረግ መብትን ያፀድቅላታል፡፡ በእስልምና ውስጥ ሴቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ሆነ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮቻቸውን በግልጽ ይከውናሉ፡፡

ለጥበቃና አንዳንድ እርዳታ አባቷ፣ ወንድሟ፣ አጎቷ፣ ወይም ባለቤቷ እንዲሁም የምትኖርበት ህብረተሰብ ግዴታ አለባቸው፡፡ በየትኛውም የእድሜ ክልሏ በአቅማቸው ልክ እና በነባራዊ ባህላዊ ተጨባጭ ክብሯን እና ማዕረጓን የመጠበቅ፣ ተገቢ የሆነ የመኖሪያ ከባቢ እንዲፈጥሩላትና የሚያስፈልጋትን እንዲያሟሉላት በህግ ተገደዋል፡፡ ይህ ደረጃዋን ዝቅ እንዲል ያደርገዋል ወይስ ከፍ?

እስልምና ወንድን ሆነ ሴቷን ከአደባባይ ብልግና ከልክሏል፡፡ ይህ ደግሞ በተፈጥሮዋዊ ምክንያት በተለያይ መልኮች ሊተረጎም ይችላል፡፡ ሁለቱም ለብቻቸው ቢሆኑ እንኳ መልካም ዕሴቶችን መጠበቅ፣ በአደባባይ ደግሞ ህየው ማድረግ አለባቸው፡፡ እስላማዊው ህግ ሴቶችን ከችግርና ትንኮሳ ይጠብቃል፡፡ ይህ ሁለቱም ፃታዎች በሴቷ ላይ ፃታዊ ጥቃት ወይም የወሲባዊ ጉትጎታ ድርጊቶችን አለማድረግ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ምክንያት ሴቷ እንደምትኖርበት አካባቢ ነባራዊ ሁኔታ የጨዋ አለባበስ እንዲለበስ፣ አላስፈላጊ የፆታ መደበላለቅ እና ወሲብ ቀስቃሽ አካላዊ መነካካት እንዳይኖር እስላማዊው ህግ ይጠይቃል፡፡

እስልምና የነፃነትን ፅንሰ ሃሳብ የሚተረጉመው ግለሰባዊ ባህሪያት/ድርጊቶች ለግለሰቡም ሆነ ለትልቁ ህብረተሰብ አጥፊ ባልሆነ መልኩ እንዲተገበሩ ነው፤ በመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ምስል ከሳች አገላለፅ እንደተነገረው፡፡

“የአላህን ህግጋት የሚጠብቅና የሚጥስ ሰው ምሳሌው በአንድ መርከብ ላይ እንደተሰባሰቡና መቀመጫቸውን በለዩ ሁለት ስብስቦች ነው፡፡ አንደኛው ስብስብ የመርከቡ የላይኛው ክፍል ይደርሰዋል፤ ሁለተኛው ስብስብ የታችኛውን ያገኛል፡፡ የታችኛው ክፍል ሰዎች ውሃ ሲፈልጉ በላይኛው ክፍል ባሉ ሰዎች መሃል ያልፉሉ፡፡ በታችኛው ክፍል ያሉ ሰዎች ለራሳቸው ‹በመርከቧ ወለል ቀዳዳ ብንሸነቁር የላይኛውን ክፍል ሰዎች ሳንረብሽ በቀላሉ ውሃ እናገኛለን› ሲሉ አሰቡ፡፡ ከላይኛው ክፍል ያሉ ሰዎች የታችኛዎቹ ዕቅዳቸውን እንዲፈፅሙ ከፈቀዱላቸው ሁሉም ይጠፉሉ፤ እንዲታቀቡ ካደረጉዋቸው ሁሉም ይድናሉ፡፡” (ቡኻሪ 2361 እና ሌሎች)

ታዋቂው ጀርመናዊው አብሰልሳይና ፈላስፋው ሾፐንሃወር (Schopenhauer) እንዲህ ይላል

*“ለሴቶች ጥቅልና ፍፁም ነፃነት ለአንድ ዓመት ስጧት እና ከእኔ ጋር ሆናችሁ የዚህን ነፃነት ውጤት ተመልከቱ፡፡ እናንተ (ሁላችሁም)፣ እኔን ጨምሮ መልካም ዕሴቶችን፣ ጥብቅነትንና መልካም ስነ ምግባራትን እንደምንወርስ እንዳትረሱ፡፡ (ቀድሜ) ከሞትኩ ‹ተሳስቶ ነበር!› ወይም ‹የእውነትን ልብ አግኝቶታል› ማለት ትችላላችሁ፡፡”*

አሜሪካዊቷ ዘጋቢ ሂሌሲያን ስታንስቤሪ (Helesian Stansbery) በ250 ጋዜጦች ላይ ለ20 ዓመታት የሠራች ጋዜጠኛ ስትሆን በርካታ ሙስሊም ሃገራትን ጎብኝታለች፡፡ በአንድ ጉብኝቷ መጨረሻ ላይ የሚከተለውን ብላ ነበር፡፡

*"እስላማዊው ዐረብ ህብረተሰብ የሞራል ይዞታውና ጤንነቱ መልካም ነው፡፡ ይህ ህብረተሰብ የወንዱንና ሴቱን በተወሰነ እና ምክንያታዊ ደረጃ ያለማደበላለቅ ባህሉን መቀጠል አለበት፡፡ ይህ ህብረተሰብ ከአውሮፓና አሜሪካ ህብረተሰብ የተለየ ነው፡፡ የእስላማዊው ዐረብ ህብረተሰብ በሴቶች ላይ የተወሰነ ገደብ የመጣል እና ለወላጆች የተለየ ክብር እና ደረጃ የመስጠት ባህል አለው...ከሁሉም አስቀድሞ ከፍተኛው ገደብ እና ወሰን የተጣለው የአሜሪካና የአውሮፓ ቤተሰብና ህብረተሰብ አደጋ ውስጥ በከተተው ገደብ የለሽ የወሲብ ነፃነት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ በእስላማዊው ዐረብ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉት ገደቦች ህጋዊና ጠቃሚም ናቸው፡፡ ባህላችሁንና የስነ ምግባር ደንቦቻችሁን እንድትጠብቁ እመክራለሁ፡፡ የሴታችሁን ነፃነት ገድቡ ወይም በተሻለ ወደ ሙሉ ፑርዳህ (ኒቃብ) ባህላችሁ ተመለሱ፡፡ የወንድና የሴት ድብልቅ ትምህርት ከልክሉ፡፡ በእውነት ይህ ከአውሮፓና አሜሪካ የወሲብ ነፃነት ይሻላችኋል፡፡ የድብልቅ ትምህርቱን ከልክሉ ያልኩበት ምክንያት በአሜሪካ እየተቸገርንበት ስለሆነ ነው፡፡ የአሜሪካ ህብረተሰብ ውስብስብ ሆኗል፤ በሁሉም አይነት*

*የወሲብ ነፃነት አይነቶችና ስያሜዎች ተሞልቷል፡፡ የወሲብ ነፃነት እና የድብልቅ ትምህርት ተጠቂዎች ወህይኒ ቤቶችን፣ መንገዶችን፣ ቡና ቤቶችን፣ የጭፈራ ቤቶችንና የሴተኛ አዳሪ ቤቶችን እየሞሉ ናቸው፡፡ ለወጣት ሴቶቻችንና ልጆቻችን የሰጠናቸው (የሐሰት) ነፃነት ወደ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ ወንጀለኛነትና እና ባርነት ለውጠናቸዋል፡፡ የድብልቅ ትምህርት፣ የወሲብ ነፃነት እና ሁሉም አይነት ‹ነፃነት› በአውሮፓና አሜሪካ ህብረተሰብ ቤተሰብን አደጋ ውስጥ ጥለውታል፤ የሞራል/ስነ ምግባር ዕሴቶቻችንን ነቅንቀውታል፡፡”*

ለሴቶች ነፃነት አቀንቃኞች የተጋፈጣቸው ጥያቄ፡- ሴቶች ራሳቸውንና ክብራቸውን፣ ማዕረጋቸውን የሚጠብቅላቸው የተሻለውና እና እጅግ ጠቃሚው ስርአት የትኛው ነው?

## የሴቶች መብቶች ጥያቄዎች

በዓለም ዙሪያ ያሉ ሴቶች የእኩል መብቶች መረጋገጥን እየጠየቁ ናቸው፡፡ በዘመናዊው ዓለም ሆነ ባለፉት ዘመናት እንደ እስላማዊው ህግ የሴቶችን እውነተኛ መብቶችን የጠበቀ፣ ያፀና እና ከለላ የሰጠ የህግ ስርአት የለም፡፡ ይህ በዚህ ምዕራፍ በተገቢ ሁኔታ ይታያል፡፡

ታዋቂው እንግሊዛዊው አብሰልሳይ ፈላስፋ ሰር ሃሚልተን (Sir Hamilton) እስልምናና የዐረብ ስልጣኔ (Islam and Arab Civilization) በሚለው መጽሐፉ የሚከተለውን አስፍሯል፡፡

*"በእስልምና ውስጥ ሴቶችን የተመለከቱ ህግጋት፣ ደምቦችና ውሳኔች የማያሻሙ፣ ግልጽና ክፍት ናቸው፡፡ እስልምና አንዲት ሴትን እንደ ግለሰብ ከሚጎዳት፣ በዝናዋና ባህሪዋ ላይ ጉዳት ከሚያደርስ ማንኛውም አይነት ሁኔታ ጥበቃ በሚያደርግ ሙሉ ክብካቤ ላይ አትኩሮት ያደረግጋል፡፡"*

ጉስታቭ ለ ቦን (Gustave Le Bon) ታዋቂ ፈንሳዊ አብሰልሳይ ነው፡፡ የአረብ ስልጣኔ (The Arab Civilization) በሚለው መፅሐፉ

*"የእስልምና የፅድቅ ተግባራት ሴቶችን በማክበር ብቻ አልተወኑም፡፡ ይልቁን እስልምና ሴቶችን በማክበር ረገድ የመጀመሪያው ሃይማኖት እንደሆነ ጨምረን መናገር እንችላለን፡፡ ይህን ከእልስምና በፊት የነበሩ ሃይማኖቶች በሴቶች ላይ ያደረሱትን ከፍተኛ ጉዳትና ነውር በማሳት ማረጋገጥ ይቻላል* (ገፅ 488)" ፅፏል፡፡

በተጨማሪም

*“በቅዱስ ቁርአን ላይ የሰፈረውና በትንታዎቹ ላይ የተብራሩትን የጋብቻ መብቶች ከአውሮፓ የባልና የሚስት የጋብቻ መብቶች በእጅጉ ይሻላሉ* (ገፅ 497)“ አመልክቷል፡፡

ከ1400 ዓመታት በፊት እስልምና ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልእክታቸውን ካስተማሩበት መካ፣ ከዚያ መዲና በመነሳት በዚያ ዘመን ታዋቂው ወደሆነው ዓለም ተስፋፍቷል፡፡ እስልምና ክርክር በሌለባቸው የህግጋቱ ምንጭ ከሆኑት መለኮታዊ ራዕይው ቅዱስ ቁርአንና መለኮታዊ ምሪቱ በነቢዩ ተግባራት የብርሃኑን አድማስ አስፍቷል፡፡ የሃይማኖቱን አስተምህሮቶችና የህግ ስርዓት በተከተሉት ህይወት ላይ መሠረታዊ የሆነ በጎ ተፅዕኖ አሳርፏል፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ሙስሊሞች የተገኙባቸው ህብረተሰቦች ሁሉ ተለውጠዋል፡፡ እስልምና እጅግ በሚያስደምም ፍጥነት በሚታወቀው ዓለም ሁሉ ሲስፋፋ የእያንዳንዱን ሰው ፍላጎት የተመለከተ የተሟላ የህይወት ስርዓት ዘርግቷል፡፡ ህይወት ለመቀጠል መሠረታዊ ከሆኑ ህጋዊ፣ ጤነኛና አሳማኝ ከሆኑ አስፈልጎቶች ጋር አይጋጭም አይቃረንም፡፡

እሰልምና ለሴቶች ያመጣውን ዙሪያ ገብ ለውጦች ለመረዳት ከሃይማኖቱ መገለጥ በፊት በዐረቡና በሌላው ዓለም ስለነበረው የሴቶች ደረጃ በአጭሩ እንመረምራለን፡፡

**የሴቶች ደረጃ በየዘመኑ**

## *ሴቶች በቀደምት እስልምና ህብረተሰብና ስልጣኔዎች ውስጥ*

በአረማዊው አረብ ህብረተሰብ ሴቶች ታላቅ በደል የደረሰባቸው ሲሆን ከአላህ መልእክተኛ መላክ በፊት ለበርካታ የተለያዩ ውርደት ተዳርገው ነበር፡፡ ወንድ ጠባቂዎቻቸው ባሰኛቸው ጊዜ እንደሚያስወግዷቸው ቁስ ነበር የሚያታዩት፡፡ ከቤተሰብ ሆነ ከባሎቻቸው የውርስ መብት አልነበራቸውም፡፡ ዐረቦች ውርስ የሚገባው ፈረስ መጋለብ የሚችል፣ የሚዋጋ፣ ምርኮ የሚማርክና የጎሳውንና ነገዱን ድንበር የማያስነካ ችሎታ ላለው ነው ብለው ያምናሉ፡፡ በአረማዊው የአረብ ህብረተሰብ ውስጥ ሴቶች እነዚህን ስለማይሠሩ እዳ ያለበት ባል ሲሞት ልክ እንደማንኛውም ተንቀሳቃሽ ንብረት አብረው ይወሰዱ፣ ይወረሱ ነበር፡፡ ባልየው ከሌላ ጋብቻ የወለዳቸው ልጆች ካሉት፣ ልጅ እንደ ከብቶች የመሳሰሉት የአባቱን ንብረቶች እንደሚወርስ ሚስቱንም እንደ አንዱ ሊደምራት ይችላል፡፡ ነፃ መውጫ ገንዘብ እስካልከፈለች ድረስ ከእንጀራ ልጇ ቤት መውጣት አትችልም፡፡

እንደ ባህል ወንዶች ያለ አንዳች ገደብ ያሻቸውን ያህል ሴቶች ማግባት ይችላሉ:: ባል በሚስቱ ላይ ጥቃት እንዳያደርስ የሚያግደው (የሚከለከለው) ምንም አይነት የህግ ስርዓት አልነበረም:: ሴቶች የትዳር አጋራቸውን የመምረጥ ነጻነት አይደለም፣ ስምምነታቸው እንኳ አይጠየቅም፤ እንደው ነበር የሚሰጡት፡፡ ባላቸው ከፊታቸው በድጋሚ እንዳያገቡ ይከለከላሉ፡፡

በቅድመ እስልምና አረማዊ የዐረብ ህብረተሰብ አባቶች ሴት ልጆች ሲወለድላቸው መናደዳቸው የተለመደ ነበር፡፡ የተወሰኑት እንደመጥፎ ዕድል ይቆጥሩታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) አባት ሴት ልጅ ሲወሰድለት ስለሚሰማው የወቅቱን ስሜት እንዲህ ይገልፀዋል፡፡

"በርሱ ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት፣ በውርደት ላይ ኾኖ ይያዘውን? ወይስ በዐፈር ውስጥ ይደብቀውን? (በማለት እያምታታ) ከሰዎች ይደበቃል፤ ንቁ፣ የሚፈርዱት (ፍርድ) ምንኛ ከፉ!" (16፡59)

ሌላው ይቅርና ሴቶች ለመዝገብ እንኳ የማይበቁ የተፈጥሮ መብቶችን ተነጥቀው ነበር፡፡ ለምሳሌ የተወሰኑ ምግቦችን እንደዳይበሉ ተከልክለዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን መዝግቦታል፡፡

«በነዚህም እንስሶች ሆዶች ውስጥ ያለው ለወንዶቻችን በተለይ የተፈቀደ ነው፡፡ በሚስቶቻችንም ላይ እርም የተደረገ ነው፡፡ ሙትም ቢኾን (ሙት ኾኖ ቢወለድ) እነርሱ (ወንዶቹም ሴቶቹም) በርሱ ተጋሪዎች ናቸው» አሉ፡፡ በመቅጠፋቸው አላህ በእርግጥ ይቀጣቸዋል፡፡ እርሱ ጥበበኛ ዐዋቂ ነውና፡፡›› (6፡139)

ዐረቦች ለሴት ልጆቻቸው ያላቸው ጥላቻ ከነሕይወታቸው እንዲቀብሩዋቸው አድርጓቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህንን ጉዳይ ከምፅዓት ቀን ጥያቄ አያይዞ አንስቶታል፡፡

“በህይወቷ የተቀበረችውም ሴት ልጅ በተጠየቀች ጊዜ፤ በምን ወንጀል እንደተገደለች” (81፡ 8-9)

ሌሎች አባቶች ሴት ልጆቻቸው የስጋ ደዌ በሽታ ወይም የአጥንት ልምሻ ካለባቸው ወይም ከሌላ የወሊድ ችግር ጋ እንደተወለዱት ይቀብራቸዋል፡፡

“ልጆቻችሁንም ድኽነትን በመፍራት አትግደሉ፤ እኛ እንመግባቸዋለን፣ (እናንተንም እንመግባለን)፤ እነሱን መግደል ኃጢአት ነውና።” (17፡31)

በቀደምት እስልምና የዐረብ ህብረተሰብ ሴቶች ማዕረግ አላቸው ከተባለ በአንድ በኩል ነው፤ ለቤተሰቧ እና ነገዷ ሲባል የሚደረግለት ግለሰባዊ ጥበቃ፡፡ እርሷን ያዋረደ ወይም ክብሯን ዝቅ ያደረገ የበቀል ጥቃት ይደርስበታል፡፡ ይህም ቢሆን የሴትነቷ ጉዳይ አሳስቦት ሳይሆን ለወንዱ ኩራትና ክብር እንዲሁም ለነገዱ ማዕረግ ሲባል የሚደረግ ነበር፡፡

ይህ የዐረብ ሴቶች ሁኔታ ሁለተኛውን የሙስሊሞች ኸሊፋ (ረ.ዐ) የሚከተለውን እንዲናገር አስገድዶታል፡፡

“በአላህ ይሁንብኝ፤ አላህ በቅዱስ ቁርአን ያነሳውን እስኪያወርድ፣ እነሱ ያከፋፈላቸውን እስክናከፋፍል ድረስ ሴቶች ምንም እንዳላቸው እናስብም ነበር፡፡” (ቡኻሪ 4269 እና ሙስሊም 31)

- **ሴቶች በህንድ ህብረተሰብ ውስጥ**

በህንድ ህብረተሰብ ውስጥ ሴቶች በጥቅሉ የሚታዩት ምንም አይነት የራሳቸው ፈቃድ ወይም ፍላጎት እንደሌላቸው አገልጋይ ወይም ባሪያ ነበር፡፡ በሁሉም ጉዳዮች ባሎቻቸውን ነበር የሚከተሉት፡፡ በቁርማር ጨዋታ የተሸነፈ ባል ሚስቱን ይከፍላል፡፡ ለባሎቻቸው ያላቸው መሰጠት ለማሳየት፣ ሚስቶች ባሎቻቸው ቀድመው ከሞቱ እና እስከሬናቸው ሲቃጠል እሳቱ ውስጥ ዘለው ይገባሉ፡፡ ተግባሩ "ሱቲ" ተብሎ የሚጠራ ሲሆን እስከ 17 መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ቀጥሎ ነበር፡፡ ይህ ልምድ ህገ-ወጥ ተብሎ ሲከለከል በሂንዱ የሃይማኖት መሪዎች ዘንድ ቁጣን ቀስቀሷል፡፡ ምንም እንኳ ሱቲ በህግ ቢከለከብልም እስከ 19 መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ተግባሩ ቀጥሏል፡፡ አሁንም ራቅ ባሉ የህንድ ገጠርማ ቦታዎች እየተተገበረ ይገኛል፡፡

በተወሰኑ የህንድ ክልሎች ደግሞ ሴቶች ለሃይማኖት መሪዎች በዕቁባትነት ወይም እንደ ሴተኛ አዳሪ ተሰጥተው ይበዛበዛሉ፡፡ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ የሂንዱ አማልክቱን ለማስደሰት ወይም ዝናብ እንዲዘንብ ይሰዋሉ፡፡ የተወሰኑ የሂንዱ ህግጋት ሁሉ ይህን ያውጃሉ፡፡

“የተወሰነ በሽታ፣ የነፋስ ማዕበል፣ ሞት፣ የገሃነም እሳት፣ መርዝ፣ እባቦች እና እሳት ከሴቶች የማያንሱ ክፉ ናቸው፡፡”

በሂንዱ የሃይማኖት መፅሐፍት ውስጥ እንዲሁ የሚከተለው ተጠቅሷል፡፡

“ማና (የሂንዱ የፍጥረታት አማልክት) ሴቶችን ሲፈጥር የፍቅር አልጋን፣ መቀመጫን፣ መጋጌጥን (ሜክ-አኘ)፣ የስጋ ቆሻሻ ፍላጎትን (ሁሉንም አይነት)፣ ንዴትን፣ በክብር እና በማዕረግ ላይ ማመጽን እና እኩይ ባህሪያትን ጸባይን እና ዝንባሌዎች ጭኖባቸዋል፡፡”

በማና ሂርማ ሊትራ አስተምሮህቶች ውስጥ ሴቶችን በተመለከተ አንባቢ ይህን ሊያነብ ይችላል፡፡

“አንዲት ሴት ትንሽ ልጅ ሆነች ልጃረገድ ወይም የበሰለች ብትሆን ያለምርጫ ትኑር፡፡ ልጃረገድ በአባቷ ምርጫ እና ትዕዛዝ ነች፡፡ ያገባች ሴት በባሏ ትዕዛዝና ምርጫ ስር ናት፡፡ ፈት ሴት በወንድ ልጆቿ ትዕዛዝና ምርጫ ስር ናት፤ ባሏ ቢሞት እንኳ ፈጽሞ ነጻ አትሁን፡፡ ፈት ሴት ከባሏ ሞት በኋላ ፈጽሞ አታግባ፡፡ ባይሆን ሁሌ እስክትሞት ድረስ የምትወደውን ሁሉ ከምግብ፣ ከአልባሳት እና መጋጌጫ ትተው፡፡ አንዲት ሴት ምንም ነገር በባለቤትነት አትያዝ ወይም የምትገኘው ነገር ካለ ወደ ባሏ በባለቤትነት ይሸጋገር ፡፡”

እጅግ ባልተለመደ ሁኔታ ሴቶች በአንድ ጊዜ በርካታ ባሎች ነበሯት፡፡ ምንም ጥርጥር የለውም ይህ በህብረተሰብ ውስጥ እንደ ሴተኛ አዳሪ አድርጓት ነበር፡፡

- **ሴቶች በቻይና ህብረተሰብ ውስጥ**

ሴቶች በቻይና ህብረተሰብ ውስጥ ዝቅተኛ እና ወረዳ ደረጃ ነበራቸው፡፡ በልማድ እጅግ የተጠሉ እና የተዋረዱ የሚባሉ ስራዎች የሚሰጣቸው ለነርሱ ነበር፡፡ ወንዱ ልጅ የሚታየው እንደ አማልክት “ስጦታ” ሲሆን እንክብካቤ የሚደረግለትም በዚያው ደረጃ ነበር፡፡ ሴቷን ልጅ በተመለከተ የተለያዩ ድርብ ድርብርብ መከራዎችን መሸከም ሲኖርባት እንደልቧ እንዳትሮጥ እግሮቿ አጣግታን ትጠቀልላቸዋል፡፡ ሌሎች ጎጂ ልማዶችም ነበሩ፡፡

አንድ የቻይኖዎች አባባል እንደሚለው “ሚስትህን ስማት፣ ነገር ግን የምትናገረዋን አትመናት፡፡”

በቻይና የሴቶች ደረጃ ከአረማዊዎቹ ዐረቦችና ከህንዶቹ ህብረተሰቦች እምብዛም የተሻለ አልነበረም፡፡

- **ሴቶች በግሪክ**

በግሪክ ሴቶች በወንዶች ምን ሳይሆኑ የዕኩይነት አይነታ እንደሆኑ እስኪቆጠሩ ድረስ እጅግ ተዋርደው ነበር፡፡ ሴቶቸን የሚጠብቅ ምንም አይነት ስርዓት አልነበረም፡፡ የመማር መብታቸው ከመነፋጉም በላይ እንደማንኛውም ሸቀኛ ይገዙና ይሸጡ ነበር፡፡ የመውረስም መብት የላቸውም፡፡ ንብረትን ሆነ ሃብትን በተመለከተ ምንም አይነት ግብይት ወይም ልውውጥ ማድረግ የማይችሉ አናሳዎች ተደርገው ነበር የሚታዩት፡፡ ፍች የወንዱ ፍጹማዊ መብቱ ነበር፡፡ በግሪክ ሲታይ የነበረው የተለመደ የሴቶች አያያዝ የተወሰነ የግሪክ አብሰልሳዩችን "ልክ እንደ ገላዋ የሴትም ስም በቤቷ ውስጥ መቆለፍ አለበት" እንዲሉ አድርጓቸዋል፡፡

ጉስታቭ ለቦን የዐረብ ስልጣኔ በሚለው መጽሐፍ ስለግሪክ ሴቶች የሚከተለው አስፍሯል፡፡

"ግሪኮች በጥቅሉ ሴቶችን የዝቅተኛ ዝቅተኛ ፍጡር አድርገው ነው የሚመለከቷቸው፡፡ ለመራባት እና የቤት ጉዳይ እንዲመለከቱ ካልሆነ በስተቀር ምንም ጥቅም የላቸውም፡፡ አንዲት ሴት "አስቀያሚ"፣ አካል ጉዳተኛ ወይም የአእምሮ ዝግመት ያለበት ልጅ ከወለደች ወንድየው (ያልተፈለገውን) ልጅ የመግደል መብት አለው፡፡

ዴሞስቴኔስ (Demosthenes) የተባለው ታዋቂው ግሪካዊ ዲስኩረኛ እና አብሰልሳይ ይህን ብሏል፡፡

“እኛ የግሪክ ወንዶች ለወሲብ ደስታ ስንል በሴተኛ አዳሪዎች አጀብ እንደሰታለን፤ “የሴት ጓደኞቻችን እና ውሽሞቻችን የዕለት ኑሯችንን ይንከባከቡልናል፤ ህጋዊ ልጆች ለማግኘት እናገባለን፡፡”

በዚህ የተንሸዋረረ ድርጊት እና የዘቀጠ ሞራል በእንደዚህ አይነት ህብረተሰብ ውስጥ ዕድልኛ የሚባሉ ሴቶች የሚገጥማቸው ነገር ከታዋቂ አብስልሳዬቻቸው መሃከል ከአንደኛው ማየት እንችላለን፡፡

- **ሴቶች በሮማውያን ህብረተሰብ**

በሮማውያን ዘንድ ሴት የራሷን ጉዳዬች ማካሄድ እንደማትችል ዝቅተኛ ፍጡር ነበር የምትታየው፡፡ ሁሉም አይነት ስልጣን የወንዱ ሲሆን የቤት የሆነ የአደባባይ ጉዳዬች በሙሉ በእርሱ ስር ነበሩ፡፡ ሚስቶቻቸው በተወሰኑ ወንጀሎች ጥፋተኞች ሆነው ከተገኙ የሞት ፍርድ እስከመስጠት መብት ነበራቸው፡፡ ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸው ስልጣን መሸጥን፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ማሰቃየትን፣ ከአገር ማበረርን እና መግደልን ያጠቃልላል፡፡ በሮማ ሴቶች ወንዶች የሚሏቸውን ማዳመጥ እና ትዕዛዛቸውን በሙሉ መተግበር ግድ ይላቸዋል፡፡ የመውረስ መብቱም አልነበራቸውም፡፡

- **ሴቶች በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ**

በባህላዊው የአይሁድ ማህረሰብ ሴቶች ከቀደሙት ህብረተሰቦች ሴቶች ዕድለኞች አልነበሩም፡፡ በብሉይ ኪዳን ሴቶች የተገለጹት በሚከተለው መልኩ ነው፡፡

አውቅና እመረምር ዘንድ፥ ጥበብንና የነገሩን ሁሉ መደምደሚያ እፈልግ ዘንድ፥ ኃጢአትም ስንፍና፥ ስንፍናም እብደት እንደ ሆነች አውቅ ዘንድ እኔ በልቤ ዞርሁ። እኔም ከሞት ይልቅ የመረረ ነገር መርምሬ አገኘሁ፤ እርስዋም ልብዋ ወጥመድና መርበብ የሆነ፥ እጆችዋም እግር ብረት የሆኑ ሴት ናት፤ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነ ከእርስዋ ያመልጣል፥ ኃጢአተኛ ግን ይጠመድባታል። (መክብብ 7፡25-26)

*"ሰውም ሴት ልጁን ለባርነት ቢሸጥ ባሪያዎች እንደሚወጡ እርስዋ አትውጣ፡፡ ጌታዋን ደስ ባታሰኘው በዎጅ ይስደዳት፤ ስለ ናቃት ለሌላ ወገን ሰዎች ይሸጣት ዘንድ አይገባውም። ለልጁም ብድራት፥ ለሴት ልጆች የሚገባውን ያድርግላት። ከእርስዋ ሌላም ቢያጋባው፥ መኖዋን ልብስዋንም ለምንጣፍዋም ተገቢውን አያጕድልባት። ይህንም ሦስት ነገር ባያደርግላት ያለ ገንዘብ በከንቱ ትውጣ።* (ዘፀአት 21፡7-11)

ስለዚህ አንዲት አይሁዳዊት ሴት ካገባች ጥበቃዋ ከአባቷ ወደ ባሏ ይዘዋወራል፡፡ እንደ ቤቱ ባሪያው አገልጋይ ወይም ገንዘቡና ሃብቱ፣ የእርሱ እንደ አንድ ንብረቱ ትሆናለች፡፡

የአይሁድ አስተምህሮዎች እና ህግጋት አባቷ ወንድ ልጆች ካሉት እርሷ እንዳትወርስ ይከለክላታል፡፡ በብሉይ ኪዳን እንዲህ ይላል

*“ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። ሰው ቢሞት ወንድ ልጅም ባይኖረው፥ ርስቱ ለሴት ልጁ ይለፍ”* (በሁልቅ 27፥8)

በተጨማሪ የአይሁድ ወንድ የወር አበባ አያየች ካለች ሴት ጋ አብሮ አይተኛም፤ አይበላም፤ ወይም አይጠጣም፡፡ ከወር አበባም ሙሉ ለሙሉ እስትጸዳ ድረስ ወንዱ ራሱን ሙሉ ለሙሉ ያገባል፡፡

- **ሴቶች በክርስትና**

የክርስትና ቄሶች ወደ ጠርዝ በመውጣት ሴቷን የውርስ ሃጢያት እና የዓለማችን እየተቸገረችበት ያለችበት ጥፋቶች ሁሉ መንስኤ ያደርጓታል፡፡ በዚህ ምክንያት ነው ወንዱ ከሴቷ ጋር

የሚያደርገው አካላዊ ግንኙነት በተለምዶ “መቆሸሽ” ተብሎ የሚጠራው፤ ምንም እንኳ ግንኙነቱ የህጋዊ ጋብቻ ቢሆንም፡፡

ቅዱስ ትሮቶሊያን (Saint Trotolian) ሲናገር

“ሴት ሰይጣን ወደ ወንዱ ልብ የሚገባበት መንገድ ናት፡፡ ሴት ወንዱን ወደ “ተረገመው” ዛፍ ትገፋዋለች፡፡ ሴት የእግዚአብሔርን ህግጋት ትጥሳለች፤ የእርሱንም አምሳያ የሰውን ምስል ታበላሻለች፡፡”

ዌት ክኑደሰን (Weith Knndesen) የተባለ ጸሐፊ በመካከለኛው ዘመን የነበረበውን የሴቶች ሁኔታ እንዲህ ገልጾታል፡፡ “እንደ ካቶሊክ እምነት ሴቷን ፣እንደሁለተኛ ዜጋ እንደሚመልከታት፣ እጅግ አነስተኛ ክብካቤና አትኩሮት ነበር የሚሰጣት፡፡”

በ1586 በፈረንሳይ ሴት ሰው ናት ወይስ አይደለችም የሚል ኮንፍረንስ ተካሂዶ ነበር፡፡ ኮንፍረንሱ የሚከተለው ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር- ሴት ሰው ናት፤ የተፈጠረችው ግን ወንዱን ለማገልገል ነው፡፡

ኮንፍረሱ ከዛ በፊት አነታራኪ የነበረውን የሴቷን የሰው ልጅነት መብት ዕልባት ሰጥቷል፡፡ ሆኖም በኮንፈረንሱ ላይ የተገኙት ለሴቷ ሙሉ መብት ሳይሆን የሰጧት መብት የሌላት፣ የወንዱ

ተከታይ እና አገልጋይ ነበር ያደረጓት፡፡ ይህ ውሳኔ እስከ 1938 ድረስ ጸንቶ ቆይቷል፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቷ የራሷን የፋይናንስ ጎዳዬች በቀጥታ እንዳታካሄድና በራሷ ስም የባንክ ሂሳብ እንዳትክፍት የሚከለክል የትኛውም አይነት የቀድም ህግ እንዲሻር የተደረገው በዚህ ዓመት ነበር፡፡

በመካከለኛው ዘመን በሙሉ አውሮፓ በሴቶቿ ላይ አድሎና መገለል ስታደርስ እና መብታቸውን ነፍጋ አሳልፋለች፡፡ የራስን ሚስት የመሸጥ መብትን በተመለከተ የእንግሊዝ ህግ በዝምታ ማለፉ ያስገርማል፡፡ በሴቶችና በወንዶች መሃከል ያለው ልዩነት እየጨመረ መጥቶ በአንድ ወቅት ሴቶች ሙሉ ለሙሉ በወንዶች ቁጥር ስር ሆነው ነበር፡፡ ሴቶች መብታቸውና በባለቤትነት የያዙት ነገር ሙሉ ለሙሉ ተገፈዋል፡፡ የሴቷ የሆነው በሙሉ የባሏ ነበር፡፡ ለምሳሌ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንደ ፈረንሳይ ህግ ሴቶች በራሳቸው የፋይናንስ ጉዳይ ውሳኔ የማሳለፍ ችሎታ እንዳልነበራቸው ይረዳገራል፡፡ 217ኛው የፈረንሳይ ህግ ማንበብ እንችላለን፡፡

“በባልና በሚስት መሃከል ሙሉ ለሙሉ ንብረታቸውን እና በባለቤትነት የያዙትን የተለያዩ ቁሳቁሶች እስካልተከፋፈሉ ድረስ፣ ፍቺም ቢኖር እንኳ፣ ያገባች ሴት ያለባሏ ተሳትፎ ወይም የተጻፈ

ፈቃድ አሳልፎ የመስጠት፣ የማስተላለፍ በክፍያ ሆነ ያለክፍያ ቦንድ ማስያዝ መብት የላትም፡፡”

ምንም እንኳ በፈረንሳይ ህግጋት ላይ በርካታ ማስተካከያዎች እና እርምቶች ቢደረግበትም፣ ይህ ህግ ያገባችን ፈረንሳዊት ሴት ምን ያህል እንደሚያስቸግራት ማየት ይቻላል፡፡ የዘመናዊ ባርነት አይነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም እንዴት ሴት ስታገባ የቤተሰቦቿን መጠሪያ አጥታ ነው ወደ ትዳሩ የምትገባው፡፡ የባሏን ቤተሰብ ስም ትሸከማለች፡፡ ይህ ደግሞ ያገባች ሴት የባሏ ተከታይ እንደምትሆና ግለሰባዊ ማንነቷን ጭምር እንደምታጣ አመልካች ነው፡፡

ታዋቂው እንግሊዛዊው ጸሐፊ ጆርጅ በርንድ ሾው “አንድ ሴት እንዳገባች በእንግሊዝ ህግ መሰረት ንብረቶቿ በሙሉ የባሏ ይሆናሉ” ብሏል፡፡

በመጨረሻም በምዕራቡ ዓለም ሴቶች ላይ የተጫነ አንድ ፍትህ የጎደለው ነገር አለ፤ እንደ ህግ እና ሃይማኖታዊ አስተምሮዎች የጋብቻ ትስስር ዘላለማዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ (ቢያንስ በካቶሊክ) የፍቺ መብት የለም፡፡ ባልና ሚስት የሚለያዩት በአካል ብቻ ነው፡፡ ሚስትየዋ ከተረፈች ከቧሏ ሞት በኋላ ድጋሚ አግብታ ትክክለኛ ህይወት መቀጠል አትችልም፡፡

ዓለምን በመቆጣጠር እየሞከረ ያለው ዘመናዊው የምዕራቡ ዓለም ስልጣኔ እየተባለ የሚጠራው ለሰዋዊው ስልጣኔው ለግሪክ እና የሮማ ባህል፣ ለርዮት ዓለሙ እና ሃይማኖታዊው መሰረቱ ለጁዶ-ክርስቲያን ባህል ባለዕዳ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ድምር ድሎችና መገፋቶች በሂደት እያደገ ከመጣው የቴክኖሎጂ እና ማህበራዊ ዝመና ተጽዕኖ ጋ ወደ ሚጠበቀውና ተፈጥሮአዊ ወደሆነው ውጤት እንዲያመራ አድርጓል፡፡ በአብሰልሳዬች መምህራን፣ ጎትጓቶች እና የስብአር እና የሴቶች መብት ተከራካሪ እክቲቪስቶች ወደሚመራ የሴቶች መብቶች የሚጠይቁ እንቅስቃሴ ተፈጠሩ፡፡ ሚዛኑ ወደ ተቃራኒው ክንድ ዞሮ ሴቶች ከወንዶች ትምህክተኛነት እና በደል ሙሉ ሙሉ ነጻ መውጣትን አጥብቀው ጠየቁ፡፡ በርግጥ በርካታ የዘመናዊው ዓለማዊ መንግስታት በስፋት የሴቶችን መብቶች አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን የዛኑ ያህል ሴቷን እንደ ወሲብ መቀስቀሻ፣ ሽያጭ፣ ውል ወይም ኪራይ ማስተላለፊያ ዕቃ እየቆጠሯት ገናና ለሆነው ኢሞራላዊ ቁሳዊ ገበያ ጥቃት አሳልፈው ሰጥተዋታል፡፡ በዚህ ምክንያት እየተኮታኮተ ያለውን ቤተሰብ ለመታደግ፣ በእጅጉ እየተስፋፉ የመጡትን ህገ ወጥ ሴሰኝነት፣ ውርጃ፣ ግብረሰዶማዊነት እና ከወሲብ ነጻነት ጋ ተያይዞ የመጡትን ወንጀሎች ለመቀልበስ በተለይ የሃይማኖት ሰዎች ቢሞክሩም ነገሮች ላይመለሱ ተከላሽተዋል፡፡

በዚህ ዓለም አቀፍ ማዕቀፍ እና ታሪካዊ ውርስ ሴቶች በእስልምና ውስጥ ያላቸውን ፍሬያማ መብቶችን አስከትለን እናቀርበለን፤ ወደ ሃይማኖቱ በተወረወሩ ስሁት ሃሳቦች ላይም ብርሃን እንፈነጥቃለን፡፡

## የሴቶች መብቶች በእስልምና፡ በጥቅሉ፤ እንደ ህጻን፣ እንደ ልጅ፣ እንደ እህት፣ እንደሚስት፣ እንደ እናት እና እንደ ዘመድና ጎረቤት

እስልምና የሴቶችን ጉዳይ የሚመለከተው ዙሪያ ገብ በሆነ መልኩ፣ ከፈጣሪዋ እና ጌታዋ አላህ ጋ ባላት ዝምድና፣ በሰውነቷ፣ እንደ ራሷና እና ተፈጥሮአዊ ጓደኛዋና የትዳር ጓደኛዋ ከሚሆነው ወንድ ጋ በሚኖራት ግንኙነት ማዕቀፍ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በምናቀርበው ጭብጥ ሴቶች በሌሎች ህብረተሰቦች ውስጥ የተረጋገጠላቸውን መብቶች እስልምና ካቀዳጃቸው ጋር እያስተያዩ ማየቱን እንዳትዘነጉ፡፡ እስልምና ከህብረተሰብ ውስጥ ደካማ እና የተገፉ ለሚባሉት፣ እየተረጋጋርን ካለንብት ጭብጥ ደግሞ ለሴቷ፣ ህይወት በሙሉ ከፍተኛ አትኩሮት እንደሚሰጥ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

## የወንዶችን የሴቶች እኩልነት በእስልምና እና የመሞላላት ያላቸው ተፈጥሮአዊ ሚና

በአንድ በኩል የወንዶች እና የሴቶች እኩልነት ምክንያታዊና ሊተገበር የሚችል ነገር ነው፤ ምክንያቱም ሁለቱም ሰዎች እንደመሆናቸው ነፍስ፣ አእምሮ፣ ልብ፣ ሳምባ ወ.ዘ.ተ አላቸውና፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተፈጥሯዊ የአካል፣ የስሜት እና የስነ ልቦና ዝንባሌ ልዩነት ስላለ የሁለቱ እኩልነት ሃሳብ ትርጉም የለሽ ስለሚሆን አይቻልም፡፡

ሁለቱ በምን መልኩ እኩል፣ በየትኛው መልኩ ተመጋጋቢ እንደሆኑ ብርሃን እንፈነጥቅበታለን፡፡

በተመሳሳይ ጾታ መሃከል- ወንድም ተሆነ ሴት- ባሉ ግለሰቦች እኩልነት እንደማይቻለው ሁሉ- በተፈጥሮ፣ የጥንካሬ እና ሌሎች መለያዎች፤ በሁለቱ ጾታዎች መሃከልም ሙሉ እኩልነት ሊሳካ አይቻልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን ውስጥ እንዳሰፈረው

“ትገነዘቡም ዘንድ ከነገሩ ሁሉ ሁለት ተቃራኒ ዓይነትን ፈጠርን፤” (51፡49)

ቅንጣቶች (Atoms) እንኳ በእሳት (ፓዘቲቭ) እና ውሃ (ነጌቲቭ) ቁራጮች (Particles) እና የኤሌክትሪክ ሃይሎች (Ions) የውሳዊ-ዝምድና እና የተመጋጋቢት ሁለትዬሽ ባህሪይ ያሳያሉ፡፡ ነገር ግን

እያዳንዳቸው የአጠቃላይ ህብር አካል ናቸው፡፡ የሁሉም ሕይወት ሁለትዮሽ መሠረት በመባል ይጠራል፡፡ አብዛኛው ህይወት ያላቸው ነገሮች ለመራባት የወንድና ሴቴን የጾታ ግንኙነት ግድ ይላሉ፡፡ የስነ ሕይወት (Biology) ትምህርት ጥናት እንደሚያስተምረን ሁሉም አጥቢ እንስሶች የጾታን ልዩነት የሚያመጡ ተመሳሳይ የሞሎኪውሎች እና ዕጢ አወቃቀር ዝርያ አላቸው፡፡ እነዚህ አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና ጾታዊ መለያዎች በሌሎች ህይወታቸውም ላይ ተፅዕኖውን በርግጠኝነት ያሳድራሉ፡፡

ወንድ ከሴቷ፣ ሴቷም ከወንዱ ፍላጎትን የማሟላት አስፈልግት ቢኖር ተፈጥሯዊ ነው፣ አንዱ ለሌላው ስለተፈጠረ፡፡ ሁለቱ ላይለያዩ ተሳስረዋል፡፡ ሆኖም ህጋዊ በሆነ መልኩ ፍላጎታቸውን እስካለሟሉ ድረስ ከግንኙነቱ የሚፈለገው ዘላቂ እርካታ ሊሳካ አይችልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው ቁርአኑ እንደሚለው

“እላንተ ሰዎች ሆይ እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤ አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤ አላህ ግልጽን ዐዋቂ፣ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።” (49፡13)

በበርካታ ሁነቶች እስልምና ሴቶችን ከወንዱ ምንም ልዩነት ሳያደርግ እኩል ያናግራቸዋል፡፡ የተወሰኑት ከስር ተዘርዝረዋል፡፡

በሚከተሉት ምዕራፎች በተለያዩ ማዕቀፎች ደግመን ደጋግመን እየተመላለስን እናብራራቸዋል፡፡

1. በሰውነት ሁለቱም- ወንዱም ሴቱም ልዩነት የላቸውም

እስልምና፣ ለምሳሌ ሴቷን አዳምን ከገነት ያስባረች፣ የውርስ ሃጢያት እና በዓለማችን ውስጥ ላሉ እኩዬች በር የቀደደች- በሌሎች ሃይማኖቶች እንደሚነገረው የፓንዶራን ሳጥን የከፈተች- አድርጎ አይመለከታትም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን እንዳስቀመጠው

“እላንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን፣ ከእርስዋም መቀናጆዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን፣ ከነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን የበተነውን፣ ጌታችሁን ፍሩ።” (4፡1)

በሌላም ቦታ ላይ ይህን ይላል፡፡

ሰው ስድ ሆኖ መትተውን ይጠረጥራልን? የሚፈስስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን? ከዚያም የረጋ ደም ሆነ፤ (አላህ ሰው አድርጎ) ፈጠረውም፤ አስተካከለውም። ከርሱም ሁለት ዓይነቶችን፣ ወንድና ሴትን አደረገ።ይህ (ጌታ) ሙታንን ሕያው በማድረግ ላይ ቻይ አይደለምን?” (75፡36-40)

አላህ (ሱ.ወ) በአንቀጾቹ ሁለቱንም ጾታዎች ከአንድ ምንጭ እንዳስገኛቸው አሳይቷል፡፡ በሰውነት መመዘኛ በሁለቱ ጾታዎች መሃከል ምንም አይነት ልዩነት የለም፡፡ የሰዎች ዝርያ ሁለት ክንፎች እንደመሆናቸው አንዳቸው ሌላውን ያሟላል፡፡ እስልምና ከእርሱ በፊት ሴቶችን የሚያዋርዱ እና በተፈጥሮም ሆነ በሌላም ባህሪያት አናሳ እንደሆነች የሚያጸድቁ ህግጋትን በሙሉ ሽሯል፡፡

"በእርግጥ ሴቶች የወንዶች መንትያ ግማሽ ናቸው፡፡" (አቡ ዳውድ 234 ፣ቲርሚዚ 113 እና ሌሎችም)

2. ከሴቷም ከወንዷም የሚጠበቁ ሃይማኖታዊ እና አምልኳዊ ግዴታዎችን በተመለከተ ምንም አይነት ልዩነት የለም

የእምነት ምስክርነት፣ ስግደት፣ የድሆች መብት ገንዘብን በመስጠት (ዘካ)፣ ጾም እና ሐጅ ለሁለቱም ጾታዎች እኩል ተደንግጓል፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች በሚገጥማቸው የተወሰኑ ችግሮች ምክንያት የተወሰኑት ለሴቶች ቀላል ይላል፡፡ በወር አበባ ጊዜ በሚከሰቱ የደም መፍሰስ እና ሌሎች የሆርሞን መለዋወጦች ምክንያት በዚህ ወቅት እንዳትሰግድ፣ እንዳትጾም ተደርጓል፡፡ ያለፏትን የጾም ቀናት የወር አበባዋ ሲያልፍ እንድታካክስ ሲጠበቅ፣ ሶላቶቿን አካክሺ ማለት ግን አላስፈላጊ ጫና ውስጥ ስለሚከታት ተትተዋል፡፡

3. ሴቶችና ወንዶች ለሚሠሩት መልካም ሥራዎች ሆነ ለሚፈፅሟቸው ወንጀሎች የሚሰጣቸው ምንዳ ሆነ ቅጣት ተመሳሳይ ነው፤ በዚህችም ምድርም ሆነ በመጪው ዓለም፡፡

በቅዱስ ቁርአን ውስጥ አላህ እንዳስቀመጠው

“ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሠራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።” (16፡97)

አሁንም አላህ (ሱ.ወ) ሲናገር

“እርሱም ያ ከችሮታው የዘላለም መኖሪያን አገር ያሰፈረን ነው፤በርሷ ውስጥ መከራ አይነካንም፤ በርሷም ውስጥ ድካም አይነካንም።” (33፡35)

4. ጨዋነትን፣ ክቡርነትን እና የግል ክብርና ማዕረግን በመጠበቅ እና በማስፋፋት ረገድ ሁለቱም ጾታዎች ተመሳሳይ የሞራል ግዴታ አለባቸው፤ መብት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በዚህ ረገድ ምንም አይነት ሁለት ምላስነት የለም፡፡ ልክ እንደወንዱ ሁሉ የጨዋ ሴት ስም የአላግባብ ከጠፉ አጥፊዎች ላይ ቅጣት ተጥሏል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአኑ እንደተናገረው

“እነዚያም፣ ጥብቆችን ሴቶች፣ (በዝሙት) የሚሰድቡ ከዚያም አራትን ምስክሮች ያላመጡ ሰማኒያን ግርፋት ግረፏቸው ከነርሱም ምስክርነትን ሁል ጊዜ አትቀበሉ፤ እነዚያም እነሱ አመጠኞች ናቸው።” (24፡4)

5. ሴቶች በፋይናንስ እንቅስቃሴ እና ንብረት በማፍራት እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማድረግ ረገድ ምንም አይነት ልዩነት አይደረግባቸውም፡፡

እንደ እስልምና ህግ ሴቶች ያለማንም ከለላ ሰጭ እና ገደብ ወይም ውሳኔ መሸጥ፣ መለወጥ እና የትኛውም አይነት የንግድ ልውውጥ ማድረግ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይህ እስከ ዘመናዊው ጊዜ ድረስ የትም ቦታ የሚታወቅ አልነበረም፡፡

6. እስልምና ሴቶችን የሚያከብር፣ ማዕረጋቸውን የሚጠብቅ እና ከእነርሱ ጋ በፍትህ እና ሀቀኝነት ግንኙነት የመያደርግን ወንድ ጤነኛ እና ጻድቅ ሰብእና እንዳለው ሲጠቁም የሚበድላቸው እኩይና ወራዳ ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ

“ከአማኞች በእምነቱ ሙሉ የሆነው በባህሪያቸው ምርጥ የሆነው ነው፤ ከእናንተ የተሻለው ለባለቤቱ መልካም የሆነው ነው” ብለዋል፡፡ (ቲርሚዚ 1162፤ የተረጋገጠ)

7. በትምህርት በመልካም አስተዳደግ እንዲሁም በእስልምና በሁለቱ ጾታዎችን መሃከል ምንም አይነት ልዩነት የለም፡፡

የአላህ መልእክተኛ በተረጋገጠ ንግግራቸው “ዕውቀት መፈለግ በእያንዳንዳ ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው፡፡” (ኢብን ማጃህ 224 እና በይሃቂ) ብለዋል፡፡

ነበዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሌላ ንግግራቸውም

“ሁለት ልጆቹን ራሳቸውን እስኪችሉ በመልካም ተንከባክቦ ያሳደገ በምጽዓት ቀን እርሱና እኔ እንደዚህ ሆነን (ሁለት ጣቶቻቸውን አጣብቀው እያሳያዩ) እንመጣለን” ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 2631)

ሴት ባሪያዎችን በተመለከተም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡

“ሴት ልጅ በእጁ ያለቸው (በባርነት የያዛት) በተገቢው ሁኔታ አስተምሮ፣ መልካም ባህሪያትን አሳይቶ እና ነጻ አውጥቶ ያገባት ድርብ ምንዳ አለው፡፡” (ቡኻሪ 97 እና ሙስሊም 154)

8. የሚኖሩበትን ህብረተሰብ የማደስና የማረም ሃላፊነት በሁለቱም ጾታዎች ላይ በእኩልነት ተጥሏል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን ውስጥ እንደገለፀው ወንዶችና ሴቶች በመልካም የማዛዝ እና ከመጥፎ የመከልከል ሃላፊነት እኩል ተሸክመዋል፡፡

“ምእምናንና ምእምናትም ከፊሎቻቸዉ ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው በደግ ነገር ያዛሉ፤ ከክፉም ይከለክላሉ፤ ሶላትንም ይሰግዳሉ፤ ዘካንም ይሰጣሉ፤ አላህንና መልክተኛዉንም ይታዘዛሉ፤ እነዚያን አላህ በእርግጥ ያዝንላቸዋል፤ አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና።” (9፡71)

9. ወንዶችና ሴቶች ዘካን እንደስሌቱ የመክፈል ግዴታም እንዳለባቸው፣ የውርስ ሃብት የሚያገኙበት የራሱ ስሌት አለው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም የእስልምና ምሁራን በአንድነት ተስማምተዋል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ሲናገር

“ለወንዶች፣ ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተዉት (ንብረት) ፈንታ አላቸው። ለሴቶች፣ም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተዉት ከርሱ ካነሰው ወይንም ከበዛው፣ ፈንታ አላቸው። የተወሰነ ድርሻ (ተደርጓል)።” (4፡7)

10. ሴቶችም እንደወንዱ ጥበቃቸውን የፈለገን የመስጠት መብት አላቸው፡፡

ቅዱስ ቁርአን እንደሚለው

“ምእምናንና ምእምናትም ከፊሎቻቸዉ ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው በደግ ነገር ያዛሉ፤”(9፡71)

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩም

“... በአንድ ሙስሊም የተሰጠ ከለላ በሁሉም ሙስሊሞች ላይ ይጸናል፣ ምንም እንኳ ከለላውን የሰጠው በደረጃው እጅግ ዝቅ ያለ ቢሆንም፡፡ በዚህ በኩል ሙስሊምን የካደ የአላህ፣ የመላእክቶች እና የሰዎችን እርግማን ይቀበላል፡፡ የትኛውም አይነት የግዴታ ወይም የውዴታ መልካም ሥራዎቹ የምፅዓት ቀን ተቀባይ አይሆኑም፡፡” (ቡኻሪ 6755)

ይህ በተቃዋቂው የዑም ሃኒ እናት ታሪክ ተረጋግጧል፡፡ ዑም ሃኒ ለአንድ ጣዖታት አምላኪ በመካ ምርኮ ጊዜ ከለላ ትሰጣለች፡፡ የእርሷ ዘመዶች (ላለፈ ጠላትነት) ሲሉ ሊገድሉት ያስፈራራሉ፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)

“ዑም ሀኒ ሆይ! አንቺ ከለላ ለሰጠሽው እኛም ከለላ እንሰጣለን” ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ 350)

እነዚህ እጅግ ባጠረ መልኩ የተነሱት የተወሰኑ መብቶች ናቸው፡፡ የእስልምና የህግ አተያየቶች ዙሪያ ገብ ተፈጥሮ እንዳቸው ያሳያሉ፡፡

## ሴቶች ጨቅላ፣ ልጆች እና ልጃገረዶች ሆነው

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን የልጆችን የመጀመሪያው መብት- አዲስ የተወለደን ልጅ የመጠበቅና የመንከባከብ ግዴታ እና አስፈላጊነት አስቀምጧል፡፡

“ልጆቻችሁንም ድኽነትን በመፍራት አትግደሉ፤ እኛ እንመግባቸዋለን፣ (እናንተንም እንመግባለን)፤ እነሱን መግደል ኃጢአት ነውና።” (17፡31)

እስልምና ወላጆችን ለልጆቻቸው ውብ ስም እንዲሰጧቸው፤ ገቢያቸውን ማዕከል ባደረገ መልኩ እንዲንከባከቧቸው፣ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሟሉላቸው፣ የጠየቁትን እንዲያቀርቡላቸው እና የተከበረና ማዕረግ ያለው ህይወት እንዲያረጋግጡላቸው ይጠይቃል፡፡

በተረጋገጠ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር

“በእርግጥ አላህ ለእናቶቻችሁ አመጸኞች እና ምስጋና የለሾች እንዳትሆኑ… ሴት ልጆቻችሁን ከነህይወቷ እንዳትቀብሩ… ከልክሏቸውን” ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ 1407 እና ሙስሊም 593)

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአንም እንዲህ ብሏል፡፡

እናቶችም ልጆቻቸውን ሙሉ የኾኑን ሁለት ዓመታት ያጥቡ፡፡ (ይህም) ማጥባትን መሙላት ለሻ ሰው ነው፡፡ ለእርሱም በተወለደለት (አባት) ላይ ምግባቸውና ልብሳቸው በችሎታው ልክ አለበት፡፡ ነፍስ ችሎታዋን እንጂ አትገደድም፡፡ ወላጂት (እናት) በልጅዋ ምክንያት ለርሱ የተወለደለትም (አባት) በልጁ ምክንያት አይጎዳዱ፡፡ በወራሽም ላይ እንደዚሁ ብጤ አለበት፡፡ (ወላጆቹ) ከሁለቱም በኾነ መዋደድና መመካከር (ልጁን ከጡት) መነጠልን ቢፈልጉ በሁለቱም ላይ ኃጢኣት የለባቸውም፡፡" (2፡233)

የእናት ጡት ከማግኘት ቀጥሎ አንድ ልጅ የሚያገኘው እጅግ አስፈላጊው መብት ክብካቤና ጥበቃ ነው፡፡ ከፍች በኋላ እናት ልጇ አስራ ሶስት ወይም አስራ አራት ዓመት እስኪደርስ/ እስክትደርስ ድረስ የማሳደግ መብት አላት፡፡ ልጆቿን እንደእናት የሚንከባከብና የሚጠብቅ እንደማይኖር ስለሚታመን እስልምና የማሳደግ መብቱን ቅድሚ ለእናት የሚሰጠው ለዚህ ነው፡፡

አብደላህ ቢን ዑምር ስለቧላ ቅሬታ ይዛ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይዛ ስለመጣች ሴት የሚከተለውን አስተላልፏል፡፡

"ልጄ ሽል ሆኖ በማህፀኔ ተሸክሜዋለሁ፤ ጨቅላ ሆኖ ጡቶቼን አጥብቼዋለሁ፤ ለበርካታ ዓመታት በታፋዎቼ ላይ ተቀምጧል፡፡ አሁን አባቱ ስለፈታኝ ልጄን ከእኔ ሊቀማ ይፈልጋል፡፡" ነቢዩም

(ሰ.ዐ.ወ) "ሌላ ስላላገባሽ ልጁን የማሳደግ ላንቺ በተሻለ ይገባሻል" ብለው መለሱላት፡፡ (አቡዳውድ 2276 እና ሌሎች)

ወላጆች ሁሉንም ልጆቻቸውን ያለልዩነት በእዝነትና በርህራሄ ማየት ግዴታ አለባቸው፡፡

አቡሁሬይራ (ረ.ዐ) ሲዘግቡ

የአላህ መልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ዐቅራዕ ኢብን ሐቢስ አት-ታማሚ ባለበት የልጅ ልጃቸውን ሐሰን ኢብን ዓሊን (ረ.ዐ) ይስሙታል፡፡ ዐቅራዕም "አስር ልጆች አሉኝ፤ አንዳቸውንም ስሜ አላውቅም" ይላቸዋል፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) አየት አድርገውት "እዝነት የሌለው እዝነት አያገኝም" ብለው ይመልሱለታል፡፡ (ቡኻሪ 5651)

እስላማዊ ህግ ለልጆቻቸው በተለይ ለሴቶች ከፍተኛ አታኩሮት እንዲሰጡ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡

"ሁለት ሴት ልጆች ያሉትና ራሳቸውን እስኪችሉ ተንከባክቦ ያሳደገ የምፅዓት ቀን እርሱ እና እኔ የምንመጣው እንዲህ ሆነን ነው፤ (ሁለት ጣቶቻቸውን አገናኝተው) ፡፡"

እስላማዊ ህግ ወላጆች ልጆቻቸው በተገቢው ሁኔታ እንዲያስድጓቸውና ጠቃሚ፣ ጤነኛ እና ትክክለኛ ትምህርት እንዲሰጧቸው ያስገድዳል፡፡

“በርሱ ክብካቤ ስር ያሉትን ሃላፊነት መተው ለሰውየው በቂ ሀጢያት ነው፡፡” (ሙስሊም 996)

ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) የአላህ መልክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር እንዲህ አስተላልፎታል፡፡

“እያንዳንዱችሁ ጠባቂ (ከለላ ሰጭ) ናችሁ፤ በምትጠብቁት ነገር ትጠየቃላችሁ፡፡ መሪ ዜጎችን ጠባቂ ነው፤ በርሱ ይጠየቃል፡፡ አንድ ሰው ለቤተሰቡ ጠባቂ ነው፤ ይጠየቅበታል፡፡ ሴቷ የባለቤቷን ቤት ጠባቂ ናት፤ በጥበቃዋ ስር ባለው ነገር ትጠየቅበታለች፡፡ አገልጋይ ለባለቤቱ ንብረት ተጠያቂ ነው፤ እንዲጠብቅ በታዘዘበት ነገር ይጠየቅበታል፡፡ እያንዳንዳችሁ ጠባቂ ናቸው፤ እንድትጠብቁት ሃላፊነት በተሰጣችሁ ነገር ትጠየቃላችሁ፡፡” (ቡኻሪ 853 እና ሙስሊም 1829)

እስልምና በሁሉም ነገር ላይ ፍትህን እንድንከተል ያዛል፡፡ ይህ ጥቅል መርህ ጾታቸው የቱ ይሁን በነርሱም ጉዳይ ላይ ይተገበራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በታላቁ ቁርአን ሲናገር

“አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም ለዝምድና ባለ ቤት በመስጠትም ያዛል፤ ከአስከፊም፣ (ከማመንዘር)፤ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፤ ትገነዘቡ ዘንድ ይገሥጻችኋል” (16፡90)

ዐይሻ (ረ.ዐ)፣ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት እና የአማኞች እናት እንዲህ ብላልኝ፡፡

አንዲት ምስኪን ሴት ሁለት ሴት ልጆቿን ይዛ ወደ ቤት መጣች፡፡ ሶስት የተምር ፍሬዎችን ስጣኋት (ሌላ የሚሰጥ ነገር አልነበረኝምና)፡፡ ለሁለቱ ልጆቿ አንድ አንድ ቴምር ሰጠቻቸውና ሶስተኛውን ልትበላው ወደ አፏ ስታስጠጋ ልጆቿ እንዳልጠገቡ ነገሯትና ተጨማሪ እንድትሰጣቸው ጠየቋት፡፡ ሴቷም ቴምሩን ለሁለት አካፍላ ሰጠቻቸው፡፡ ሴትየዋ ያደረገችውን ነገር አድንቄ ታሪኩን ለአላህ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ነገርኳቸው፡፡ ታሪኩን ከሰሙ በኋላ “በዚህ ድርጊቷ አላህ ገነትን ግድ አደረገላት ወይም በዚህ ተግባሯ ከገሃነም እሳት አዳናት” አሉ፡፡ (ሙስሊም 2630)

በሌላ የተረጋገጠ ሐዲስ መጨረሻ ላይ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

“ሴት ልጆችን (የማሳደግ ሃላፊነት) ተሰጥቶት ሁለቱንም በቸርነት ከተንከባከባቸው ከጀሃም እሳት ጥበቃ ይኖረዋል፡፡” (ቡኻሪ 1352 እና ሙስሊም 2629)

እስልምና ወላጆች ጾታ ሳይለዩ ለልጆቻቸው በቁስ ሆነ በስሜት ሚዛናዊ ዕይቴ እንዲኖራቸው ያሳስባል፡፡ ወንድ ልጅ ከሴቷ፣ ሴቷም ከወንዱ በተለየ መልኩ መታየት የለባቸውም፡፡

የአላህ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ለአንድ ልጅ ስጦታ ለሚሰጠው ባልደረባቸው "ለሁሉም ልጆችህ ይህ ታደርጋለህ?" ሲሉ ይጠይቁታል፡፡ "አላደርግም" ሲል ይመልስላቸዋል፡፡ እርሳቸውም "አላህን ፍራ! ለሁሉም ልጆችህ ፍትሃዊ ሁን" ብለውታል፡፡ (ሙስሊም 1623)

እስልምና ለወላጅ አልባ ልጆችን ክብካቤ ማድረግ ከፍተኛ አትኩሮት ሰጥቷል፡፡ ወላጅ አልባ መሆን በልጁ አእምሮዋዊ፣ መንፈሳዊ እና የስሜት ሁኔታ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ በመሆኑም ለወላጅ አልባ ህጻናት ወንድም ሆኑ ሴት ከፍተኛ አትኩሮ ተሰጥቷል፡፡

የልጁ የቅርብ ቤተሰብ እንዲንከባከበው ይጠይቃል እስልምና፡፡ ምንም አይነት ዘመድ ከሌለው ልጁን የመንከባከብ እና የሚያስፈልጋቸውን የሟሟላት ሃላፊነት የመንግስት ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በተከበረው ቁርአን እንዲህ ይላል፡፡

"የቲምንማ አትጨቁን።" (93፡9)

እንዲሁም በተጨማሪ

“እነዛ የየቲሞችን ገንዘብ በመበደል የሚበሉ በሆዶቻቸው ውስጥ የሚበሉት እሳትን ብቻ ነው፤ እሳትንም በእርግጥ ይገባሉ። (4፡10) ብሏል፡፡

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) አጽዕኖት ሰጥተውበታል፡፡

“አላህ ሆይ! በሁለት ደካሞች ላይ የማይጣስ መብቶች አውጇያለሁ፤ ለወላጅ አልባዎች እና ሴቶች፡፡” (ሃኪም 211 እና ጠባራኒ)

በህብረተሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች እንደደካማ በሚታዩት በሁለቱ ላይ የትኛውም አይነት ጉዳት ወይ ኢፍተሃዊ ነገር ማሰብ ታላቅ ሃጢያት እንደሆነ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እየጠቆሙ ነው፡፡

በሌላ ንግግራቸውም እንዲሁ

“ጥፋት ከሚያስከትሉ ሰባት ታላላቅ ሃጢያቶች ራቁ” አሉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም “የአላህ ነብይ ሆይ! እነዚህ ሃጢያት ምንድናቸው?” ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ “በአላህ ላይ ሌላ ማጋራት፣ ጥንቆላ፣ ያለምንም ፍትሃዊ ምክንያት የሰው ህይወት ማጥፋት፣ አራጣ መብላት፣ የወላጅ አልባ ልጆችን ሃብት መንጠቅ፣ ከጦር ሜዳ መሸሽ እና ንጽህ፣ ጥብቅ እና አማኝ ሴትን በዝሙት መጠርጠር” ብለዋል፡፡

ወላጅ አልባ ልጆችን በመንከባከብ ረገድ አማኝ ሙስሊሞችን አብዝተው የሚሳስቡ በርካታ ነቢያዊ ንግግሮች ተዘግበዋል፡፡ ለምሳሌ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)

“እኔና የወላጅ አልባ ልጅ ተንከባካቢ በገነት እንዲህ ነን” ብለዋል- ጠቋሚ እና መሀል ጣቶቻቸውን አቆላልፈው እያሳዩ፡፡

የራሳቸው ምንም አይነት አንዳች ጥፋት በሌለበት ወደዚህች ዓለም በህገ-ወጥ መንገድ ለተቀላቀሉ ልጆች ደህንነት እስልምና በእጅጉ ያስባል፡፡ እንደወላጅ አልባ ልጆች መንግስት የህብረተሰብ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ክብካቤ ያደርጋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የአዛኝነትን ጥቅል መመሪያ እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡ “...ህይወት ላለው ፍጡራን በሙሉ (ለሠራችሁት መልካም ስራ) ምንዳ አላችሁ፡፡” (ቡኻሪ 2334)

ሴት ልጅ ለአቅመ ትዳር ስትደርስ አባት (ወይም ጠባቂዋ) አስተያየቷን የመጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡ የእርሷ አስተያየት ለትዳሩ መመስረት ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የትኛውም አይነት ማስገደድ ህገ-ወጥ ሲሆን የቀረበላትን የትዳር ጓደኛ የመቀበል ወይም የትዳሩንም ጉዳይ ጭራሹኑ እርግፍ አድረጋ የመተው መብት አላት፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.0.ወ) እንዲህ ብለዋል

“ፈት ወይም ባለቤቷ የሞተባት ሴት ያለፍቅዷ ልትገባ አይገባም፤ ድንግልም ይሁንታዋን ሳትሰጥ ትዳር ውስጥ መግባት የለባትም፡፡” እነሱም “የአላህ መልክተኛ ይሁንታዋን እንዴት ትስጥ?” ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ እርሳቸው “ዝም ትላለች (ከእፍረቷ የተነሳ፤ ነገር ግን አለመስሟሟቷን ካልገለጸች)” ብለው መልሰዋል፡፡ (ቡኻሪ 4843)

አንዲት ሴት ወደ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ) ጋር ትመጣና

“የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በሰዎች ዘንድ ያለውን ደረጃ ከፍ ለማድረግ ሲል አባቴ ከወንድሙ ልጅ ጋ ትዳር እንድመሰርት አደረገኝ” ትላቸዋለች፡፡ የአላህ መልክተኛም (ሰ.0.ወ) ትዳሩን እንድትቀበለው ወይም እንድትተወው ጉዳዩን ለእርሷ ሰጧት፡፡ ሴትየዋው “አባቴ የሠራውን እቀበላለሁ፡፡ ነገር ግን ለሌሎች ሴቶች በዚህ ጉዳይ ላይ አባቶቻቸው (የፈለጉትን ሰው እንድታገባ የማስገደድ) መብት እንደሌላቸው እንዲያውቁ ፈልጌ ነው” አለች፡፡ (አህመድ 25027)

ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ) እንደተናገሩት ሴት ልጆች ዋጋ ሊወጣላቸው የማይችሉ ውድ ናቸውና፡፡

“ሴት ልጆችንና ልጃገረዶችን አታስገድዷቸው፤ ውድ እና አስደሳች ባልደረባ ናቸውና፡፡” (አህመድ 17411 እና የተረጋገጠ)

- **የሴቶች እንደ ሚስት**

ጥራት የተገባው አላህ በተከበረው ቁርአን እንዲህ ይላል

“ለናንተም፣ ከነፍሶቻችሁ (ከጐሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፤ በዚህ ውስጥ ለሚያስውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ።” (30፡21)

ከአላህ (ሱ.ወ) ታላላቅ ምልክቶች መሃከል አንዳቸው በሌላኛው ምቾት እንዲያገኙና እንዲረዳዱ አንዱን ለሌላው ጥንድ አድርጎ መፍጠሩ ነው፡፡

የህብረተሰብ ዋና መሠረት ቤተሰብ ነው፡፡ ባልና ሚስት ቤተሰብ የሚቆምበት ጥንድ ሞልታዎች ናቸው፡፡ ለቤተሰብ ስኬት፣ ለቤቱ ስክነት እንዲበዛ እስልምና ለጥንዶቹ የተወሰኑ መብቶችና ግዴታዎች አስቀምጧል፡፡ በዚህ ክፍል በሚስትየዋ መብቶች ላይ እናተኩራለን፡፡

**ጥሎሽ፡** ጥሎሽ የእያንዳንዷ ሙሽራ መብት ነው፡፡ ጥሎሽ እስካተቆረጠና እስካልተሟላ ድረስ ጋብቻ ህጋዊ አይሆንም፡፡ ሙሽሪት ብትፈቅድ እንኳ የጋብቻ ኮንትራቱ እስካልተሟላ ድረስ መብቱ አይታለፍም፡፡ የጋብቻ ኮንትራቱ ከተፈጸመ በኋላ ጥሎሽ የሚስትየዋ ብቻ ሲሆን ያለጠያቂ የፈቀደችውን ልታደርግበት ትችላለች፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን እንዳሰፈረው

"ሴቶችንም መህሮቻቸውንም በደስታ ስጡ፤ ለናንተም ከርሱ አንዳችን ነገር ነፍሶቻቸው ቢለግሱ፣ መልካም ምስጉን ሲሆን ብሉት።" (4፡4)

ትዳሩ ባይሰምርና ፍቺ ቢከሰት ባልየው ለጥሎሽ ከሰጠው ሰባራ ሳንቲም እንኳ መንጠቅ አይፈቀድለትም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዳለው

"በሚስትም ስፍራ ሚስትን ለመለወጥ ብትፈልጉ፣ ለአንደኛዪቱ (ለምትፈታው) ብዙን ገንዘብ የሰጣችኋት ስትሆኑ ከርሱ ምንንም አትውሰዱ። በመበደልና ግልጽ በሆነ ኃጢያት ትወስዱታላችሁን? ከፊላችሁ ወደ ከፊሉ በእርግጥ የደረሰ ሲሆንና ከናንተ ላይም (ሴቶች) የጠበቀ ኪዳንን የያዙባችሁ ሲሆኑ እንዴት ትወስዱታላችሁ!" (4፡20-21)

አንቀጹ የትዳር ቃል ኪዳንን ጥብቅነትን፣ የጋብቻ ግንኙነት ቅርብነትን እና በፍቺ ጊዜ ጥሎሽን የማስቀረት መብትን በጉልህ ያሳያል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በተጨማሪ ሲናገር

“እላንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ሴቶችን ያስገደዳችሁ ሆናችሁ ልትወርሱና ግልፅን መጥፎን ስራ ካልሠሩ በስተቀር ከሰጣችኋቸው ከፊሉን ልትወስዱ፣ ልታጉላሏቸውም ለናንተ አይፈቀድም፤ በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፤ ብትጠሉዋቸውም (ታገሡ)፤ አንዳችን ነገር ልትጠሉ አላህም በርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይቻላልና።” (4፡19)

ሰውየው ሚስቱን ለየትኛውም ምክንያት ቢጠላት የሚስትየው መብት እና ሙሉ ፍትህ በአንቀጹ ተረጋግጧል፡፡ አቡሁረይራ (ረ.ዐ) ባስተላለፉት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ተመሳሳይ ሃሳብ ተንጸባርቋል፡፡

“አንድ አማኝ አማኝ ሴት (ሚስቱን) መጥላት የለበትም፡፡ አንዱን ባህሪ ቢጠላው በሌላው ይደሰታል፡፡” (ሙስሊም 1469)

**የገንዘብ እርዳታ፡** እንደደረጃውና ሥራው ባል ለቤቱ በቂና መልካም ቀለብ መስፈር አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንደሚለው

“የችሎታ ባለቤት ከችሎታው ይቀልብ፤ በርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበበት ሰው አላህ ነፍስን የሰጣትን እንጅ አያስገድድም፤ አላህ ከችግር በኋላ ምቾትን በእርግጥ ያደርጋል።” (65፡7)

በቂ ሃብት ያለው ባል በእርሱ ደረጃ መስጠት የሚገባውን ካልሰጠ ሚስትየዋ የእርሷንና የልጆቿን መሠረታዊ ፍላጎት ያሚላል ብላ ያሰበችውን ከኪሱ መውሰድ ትችላለች፡፡

ሂንድ ቢንት ዑትባህ ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ትመጣና "ባሌ ንፉግ ነው፤ ለእኔም ለልጆቹም በቂ ብር አይሰጥም" ትላቸዋለች፡፡ እርሳቸውም ሲመልሱ "ለአንቺ እና ለልጆችሽ የሚያስፈልጋችሁን ያህል መጠን ሳታልፊ ውሰጅ" ብለዋታል፡፡ (ቡኻሪ 5049)

ባልየው በከፍተኛ የገንዘብ ችግር ውስጥ ከሆነና የቤተሰቡን የገንዘብ ፍላጎት ካላሟላ ወይም ረዘም ላለ ጊዜ ባለቤቱን ጥሎ ከሄደና እርሷ ችግር ውስጥ ከገባች ሚስትየዋ ፍርድ ቤት ጣልቃ እንዲገባ መጠየቅ፣ ትዳሩም እንዲቋረጥ ከፈለገችም ትችላለች፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለባልደረባቸው ሰዓድ ኢብን አቢ ወቃስ (ረ.ዐ) እንዲህ ብለውታል፡፡

"ከአላህ ምንዳን ፈልገህ በቤተሰብህ ላይ የምታወጣው የትኛውም አይነት ገንዘብ አላህ (ሱ.ወ) ይመነዳሃል፤ ለሚስትህ ለምታጎርሳት አንዲት ጉርሻ እንኳ፡፡"

**ፍትህ ፣እኩልነት እና ሚዛናዊነት፡** ከአንድ በላይ ያገቡ ወንዶች ሚስቶቻቸውን በተመለከተ በፍትህ፣ እኩልነት እና ሚዛናዊነት

መንከባከብ አላቸው፡፡ ይህ መጠለያን፣ አልባሳትን፣ ቀለብን እና ጊዜውን፤ ሃሳቡን እና የቅርብ ግንኙነትን ያጠቃልላል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ሲናገር

"ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስትም፣ አራት አራትም አግቡ። አለማስተካከልንም ብትፈሩ፣ አንዲትን ብቻ፣ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን ያዙ፤ ይህ ወደ አለመበደል በጣም የቀረበ ነው።" (4፡3)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያስጠነቅቁ

"ሁለት ሚስቶች ያሉት ወንድ በሁለቱ መሃከል ፍትህ ያጓደለ ከሆነ የምጽዓት ቀን አንደኛው ጎኑ ሽባ ሆኖ ይመጣል፡፡" (አቡዳውድ 2133 እና የተረጋገጠ)

ይህ አንድ ባል በሚስቶቹ መሃከል ፍትህ፣ ሚዛናዊነት እና እኩልነት ማረጋገጥ እንዳለበት ያሳያል፡፡ በዚህ ምድር በአንደኛው ሚስቱ መብቶች ላይ ጉድለት ስላደረሰ በሚቀጥለው ዓለም በእርሱ ላይ ጉዳት ይከሰታበታል፡፡

አንድ ባል ሚስቱን በየትኛውም መንገድ ማዋረድ፣ ማሰቃየት፣ መረበሽ፣ ያልተገባ ጫና ውስጥ መክተት፣ መስደብ፣ መደብደብ በገንዘቧ ላይ ጉዳት ማድረስ እና ከቤት እንድትወጣ ማድረግ

በእስልምና ክልክል ነው፡፡ በተለይ ለፍች ሃብትና ንብረቷን መደርደሪያ ማድረግ ተወግዟል፡፡

**ጥበቃና መከላከል፡** አንድ ባል ሚስቱንና ልጆችን የአቅሙን ያህል ሊጎዳቸው ከሚችል ነገር ወይም ኢሞራላዊ ተግባራት መጠበቅና መከላከል አለበት፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ሲናገር

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና በተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችን ደንጊያዎች ከሆነች እሳት ጠብቁ፤ በርሷላይ ጨካኞች፣ ኀይለኞች የሆኑ መላእክት አሉ፤ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጡም፤ የሚታዘዙትን ሁሉ ይሠራሉ።" (66፡6)

ህገ ወጥ እና አሳፋሪ ከሆኑ ተግባራት መጠበቅ የሚደገፍ ሲሆን ድንበር ማለፍ ግን ተገቢ አይደልም፡፡

**ወዳጅነት፣ ክብካቤ እና ቅርብ ግንኙነት፡** ባል ከሚስቱ ጋር በማዕረግ በመልካምነት እና ከበሬታ መኖር አለበት፡፡ ቤት ሲሆን እርሱ ሚስቱ እንድትሆንለት የሚፈልገውን እርሱም ለእርሷ መሆን አለበት፡፡ ንጽህ እና ተቀባይነት ያለው አለባበስ ሊኖረው ይገባል፡፡

የአላህ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ መልካም ባህሪይ እና ጠባይ መላበስ አጠቃላይ መርህ ሲያብራሩና ሲያበረታቱ

“ከአማኞች እምነቱ የሞላው መልካም ባህሪይ ያለው ነው፤ ከእናንተ በላጩ ለሚስቱ ምርጥ የሆነው ነው፡፡” (ቲርሚዚ 1162 እና የተረጋገጠ)

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የራሳቸውን ልብስ ይጠቅሙ፣ ጫማቸውን ያድሱ፣ ሚስቶቻቸውንም በቀን ሥራዎቻቸው ያግዙ ነበር፡፡

የእርሳቸው ባለቤት ዐይሻ (ረ.ዐ) አንድ ጊዜ “የአላህ መልእክተኛ ቤታቸው ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ምንድነው የሚሰሩት?” ተብለው ተጠይቃው፣ “ቤተሰባቸውን ያገለግሉና ይረዱ፣ የስግደት ጥሪ አዛን ሲሰሙ ሊሰግዱ ይሄዱ ነበር” ብላ መልሳለች፡፡ (ቡኻሪ 644)

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሁልጊዜ ተጫዋች፣ መልካም እና ተንከባካቢ ነበሩ፡፡ ከቤተሰቦቻቸው በጨዋነት ይቀላለዳሉ፡፡

“አንድ መስሊም ወንድ የሚያጠፋው ሥራ አልባ ጊዜ ውሸት ነው፣ ቀስት ከመወርወር፣ ፈረሱን ከመግራትና ከባለቤቱ ጋር ከመጨዋወት ያሉት ሲቀሩኝ፡፡ እነዚህ ከእውነት ናቸውና፡፡” (ነሳዒ 8939 እና የተረጋገጠ)

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከቤተሰባቸው ጋር ጊዜ ሲያሳልፉ በጨዋታ አዋቂነታቸውና አዝናኝነታቸው ይታወቃሉ፡፡ ከነዚህ የተዝናኖት ጊዜያት መካከል ከአይሻ (ረ.ዐ) የሚያሳለፉት ጊዜ ይታወሳል፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እና ባለቤታቸው አይሻ (ረ.ዐ) ጋ አንድ ጊዜ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ አይሻ በመቀጠል ስትናገር “ከነብዩ ጋ የሩጫ ውድድር አደርግን እና እኔ አሸነፍኩ፡፡ አረፍ ብዬ ድጋሚ ሩጫ ስንወዳደር እርሳቸው አሸነፉኝ፡፡ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ውድድሩን እንዳሸነፉ ‹አንቺ ያሸነፍሽውን በዚህ አካካስሁ› አሉኝ፡፡” (አህመድ 26320)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የምሽት ሰላታቸውን ከሰገዱ በኋላ ወደ እንቅልፍ ከመሄዳቸው በፊት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይጨዋወቱ እንደነበረም ተዘግቧል፡፡

ኢብን አነስ (ረ.ዐ) እንደተናገረው “የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሌሊት አምልኮት ለማየት አንድ ሌሊት በመይሙናህ በነቢዩ ባለቤት ቤት አደርኩ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ከባለቤታቸው ጋ ከተጨዋወቱ በኋላ እንቅልፍ ተኙ፡፡ ከሌሊቱ ወደኋላ ተነስተው አላህ የጻፈላቸውን ሰገዱ፡፡” (ቡኻሪ 93 እና ሙስሊም 763)

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን ሲናገር

“ለናንተ፣ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፥ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፣ በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል አላችሁ፤” (33፡21)

በመሆኑም የአላህ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) አማኞች በሙሉ እንዲከተሏቸው የተገቡ አይነታ አርአያችን ናቸው፡፡

የሚስትን ሚስጢር መጠበቅ ድክመት ካለባት ድክመቷን ሊሸፍን ግድ ነው፡፡ የትኛውም አይነት የግል ጉዳያቸውን ለአደባባይ መውጣት የለበትም፤ በቅርብ ጓደኞሞች ጨዋታ መሃል ቢሆንም፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያስጠነቅቁ

በምጽዓት ቀን በአላህ ዘንድ ከተጠሉ ሰዎች መሃከል አንዱ ከሚስቱ ጋ የስጋ ግብር አድርጎ ምስጢሯን የሚያወጣ ነው ብለዋል፡፡ (ሙስሊም 1437)

ሌሊቱን ከባለቤቷ ጋር የማሳለፍ፣ የስጋ ግብር የማድረግና በርሱም የመደሰት ያገባች ሴት መብት ሲሆን ይህ መብት በእስልምና ትልቅ አትኩሮት ከተሰጣቸው መሃከል ነው፡፡ ባልየው በእስላማዊ ህግ የባለቤቱን የግብረ ስጋ ግንኙነት መብት እንዲጠብቅ ይገደዳል፡፡ ሚስት እንደማንኛውም ሴት የመፈቀር፣ በልዩ አይን የመታየት፣ እንክብካቤ የመሻት እና የተፈጥሮ አካላዊ ምኞቶቿን የመወጣት ከፍተኛ ፍላጎት አላት፡፡

ባሎች የሚስቶቻቸውን የትኛውም አይነት ፍላጎቶች እንዲያሟሉ በሚያዘናጓቸው ተግባራት ውስጥ መጠመድን፣ አምልኮዎች ቢሆኑ እንኳ ከልክሏል፡፡ ሰልማን አልፋሪስ (ረ.ዐ) ታዋቂ ገጠመኙን እንዲህ ይተርከዋል፡፡

የእምነት ወንደሜን አቡ ደርዳን (ረ.ዐ) ልጎበኝ ወደቤት ሄድኩኝ፡፡ እንደደረስኩ ባለቤቱ ዑሙ ደርዳ ተቀበለችኝ፡፡ ራሷን ጥላ አገኘኋት፡፡ ይህን እንዳየሁ "የሆንሽው ነገር አለ እንዴ? ለምንድነው በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ያለሽው? ለባለቤትሽስ ራስሽን ጣል ጣል ያደረግሽው?" አልኳት፡፡ እርሷም "ወንድምህ አቡ ደርዳ ከዚህች ዓለምና ጉዳይዋ ፍላጎት የለውም፡፡ ሌሊቶችን እየሰገደ፣ ቀኖቹን እየጾም ነው የሚያሳልፋቸው" ብላ መለሰችልኝ፡፡ አቡ ደርዳ እንደመጣ ሰላምታ ተለዋውጠን የሚበላ አቀረበልኝ፡፡ "ለምን ከእኔ ጋ አትበላም?" ስል ጠየቅሁት፡፡ አቡ ደርዳም "እየጾምኩ ነው" ሲል መለሰልኝ፡፡ "በአላህ ጾምህን ፈተህ ከእኔ ጋ መብላት አለብህ" አልኩት፤ አቡ ደርዳም ጾሙን ፈትቶ ከእኔ ጋ በላ፡፡ ለሊቱንም በዚያ አሳለፍኩ፡፡ የለሊት ስግደትን ሊሰግድ አቡ ደርዳ ሲነሳ ከለከልኩት፡፡ "አካላትህ በአንተ ላይ የተወሰኑ መብቶች አላቸው፤ አምላክህ በአንተ ላይ የተወሰኑ መብቶች አለው፤ ቤተሰብህ በአንተ ላይ የተወሰኑ መብቶች አላቸው፡፡ የተወሰኑ ቀናት ጹም በሌሎች ቀናት ጾምህን ፍታ፤ ወደባለቤትህም ቅረብ፡፡ ለእያንዳንዱ መብታቸውን ስጣቸው"

አልኩት፡፡ ሊነጋጋ ሲል ለአቡ ደርዳ ፈቅጄለት ሁለታችንም ተነስተን ወዱዕ አድርገን ከሰገድን በኋላ የፈጅር ሶላት ለመስገድ ወደ መስኪድ ሄድን፡፡ ከአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋ ሰገድን ከጨረስን በኋላ አቡ ደርዳ ስለገጠመኙ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ነገራቸው፡፡ የአላህ መልክተኛም "ሰልማን እውነት ተናገረ" አሉ፡፡ (ቡኻሪ 1867)

የሚስቱን ፍላጎቶች ለመጠበቅ ባል ረዘም ላለ ጊዜ ከባለቤቱ መለየት የለበትም፡፡ ኸሊፋው ዑመር ኢብን አል ኸጣብ (ረ.ዐ) ከሴት ልጁ ሀፍሷ ጋር አንዲት ሴት ከባሏ ተለይታ ለምን ያህል ጊዜ በትእግስት ጠብቃ መቆየት እንደምትችል መክሮ የዘመቻ ቆይታ ስድስት ወር እንዲሆን ወስኗል፡፡

ይህ ጊዜ አማካኙ ሲሆን ሁኔታዎች እንደፈቀዱ ቆይታው ከዚህ ጊዜም ሊያንስ ወይም ሊበልጥ ይችላል፡፡ ስለሆነም ሚስቱ ባለቤቷን ከስድስት ወር በላይ ልትጠብቀው ወይም ከዚያ በፊት እንዲመለስ ልታደርገው ትችላለች፡፡

ባል አሳማኝ ምክንያት እስከሌለው ድረስ የሚስቱን ጥያቄ አለመቀበል አይችልም፡፡ ሚስትዬው ፍቃድ እስካልሰጠችው ድረስ እሷን ወክሎ ምንም አይነት የገንዘብ ነክ ጉዳይን መወሰን የለበትም፡፡ የሷንም ሀብት እስካላፀደቀች መውሰድ ክልክል ነው፡፡

ትላልቅ ቤተሰባዊ ውሳኔዎችን- የልጆችን ጉዳይ እና ሌሎችን በጋራ የሚመለከታቸውን- ያለ እርሷ ተሳትፎ ማሳለፍ የለበትም፡፡ የቤቱ አባወራ የተቀሩ የቤተሰቡን አባላት ሀሳብ ሳያዳምጥ በእርሱ ሀሳብ ብቻ እንዲመሩ ማድረግ ከጥበብ አይደለም፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ጉዳይ ላይ የማይረሳ ምሳሌ አሳይተውናል፡፡

በሁዴብያ ስምምነት ቀን የአላህ መልክተኛ ባልደረቦቻቸውን ከ"አህራም" እንዲወጡ ፀጉሯቸውን እንዲላጩ ያዟቸዋል፡፡ ባልደረቦቻቸው ትዛዛቸውን አልተገበሩም፡፡ ባለቤታቸው ዑሙ ሰላማህ (ረ.ዐ) ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው ፁራቸውን ተላጭተው እንዲወጡ ትመክራቸዋለች፡፡ ነቢዩም የባለቤታቸውን ምክር ተቀብለው ተገበሩት፡፡ ባልደረቦቻቸውም ትእዛዙን ለመፈፀም መቻኮል ጀመሩ፡፡

ባል የሚስቱን ስህተት ማነፍነፍ የለበትም፡፡ ለምሳሌ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ብለዋል፡፡ "ባል ከጉዞ ወደ ቤቱ አምሽቶ (መምጣቱ ቀድሞ ሳያሳውቅ) አይምጣ፡፡" (ቡኻሪ 4948 እና ሙስሊም 715)

ጃቢር ሲናገር "የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ባል ታማኝነታቸውን እንደሚጠራጠር እና እንዲመሰልላቸው እንደ ለሊት ጎብኚ ወደ ቤተሰቡ እንዳይመጣ ከልክለዋል፡፡" (ሙስሊም 715)

ባል ለሚስቱ መልካም፣ ፍላጎቷን ለማሟላት የተጋ፣ ቸር እና ተንከባካቢ መሆን አለበት፡፡ ባል ፍቅሩን፣ ውዴታውን፣ አድናቆቱን፣ አሳቢነቱንና እውነተኛ ቀረቤታውን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ተፈጥሮአዊ ማንነቷን ማስተዋል አለበት፡፡

የእስልምና የፍች ስርአት የሴቷን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ የእርቅንም እድል ማስፋት ያለመ ነው፡፡ ወደፊት በዝርዝር የምናየው ሲሆን እዚህ የተወሳበት ምክንያት እንደ ትዳሩ ሁሉ ፍችውም በጤዋ ሁኔታ የሁለቱም ወገን መብት ባስጠበቀ መልኩ መፈፀም እንዳለበት ለማስታወስ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዳለው

“ፍች ሁለት ጊዜ ነው፤ (ከዚህ በኋላ) በመልካም መያዝ ወይም በበጎ አኳኋን ማሰናበት ነው፡፡ የአላህንም ሕግጋት አለመጠበቃቸውን ካላወቁ በስተቀር ከሰጣችኋቸው ነገር ምንንም ልትወስዱ ለእናንተ (ለባሎች) አይፈቀድላችሁም፡፡ የአላህንም ሕግጋት አለመጠበቃቸውን ብታውቁ በእርሱ (ነፍሷን) በተበዠችበት ነገር በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለም፡፡ ይህች የአላህ ሕግጋት ናት፤ አትተላለፏትም፡፡ የአላህንም ሕግጋት የሚተላለፉ እነዚያ እነርሱ በዳዮች ናቸው፡፡” (2፡ 229)

## ሴቶች እንደ እናት

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን በተደጋጋሚ ስለወላጆች መብት በጥቅሉ፣ የእናትን ደግሞ በተለየ አትኩሮት ሰጥቶ ተናግራል፡፡

“ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፦ እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፤ በአንተ ዘንድ ሆነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፤ አትገላምጣቸውም፤ ለነርሱም መልካምን ቃል ተናገራቸው።” (17፡23)

በዚህ አንቀፅ የአላህ አምልኮ ከወላጆች ሀቅ በተጓዳኝ ቀርቧል፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ምሁራን የወላጆች መብት ከአላህ በስተቀር ከሁሉም በላይ ሆኖ እንደሚቀመጥ ተስማምተዋል፡፡

ወላጆችን መታዘዝ ከሁሉ ነገር- ሚስትም ጨምሮ- ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ ይህ ግን ሚስት ትዋረዳለች ወይም ዋጋ የላትም ማለት ሳይሆን ወላጆች በአላህና በነብዩ (ሰ.0.ሰ) ማመፅን እስካላዘዙ ድረስ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ማለት ነው፡፡

አላህ በአንድ ሰው የመደሰቱ ወይም አለመደሰቱ የወላጆቹ መደሰትና አለመደሰት ምክንያት ነው ነብዩ (ሰ.0.ወ) እንደተናገሩት፡፡

“የአምላክ ደስታ በወላጆች ደስታ ነው፡፡ የአላህ ንዴት በወላጆች ንዴት ነው፡፡” (ኢብን ሐንበል 429 እና ጠበራኒ፤ የተረጋገጠ)

“ቢር አል-ወሊደይን”- ለወላጆች፣ በተለይ በአቅመ ደካማነታቸው ጊዜ ታዛዥ፣ መልካምና ጥሩ መሆን፤ እነሱን ማስደሰትና መንከባከብ ማለት ነው፡፡ እነርሱን ማገልገል የግዴታ አገልግሎት ሲሆን ከሌሎች በርካታ እንደ ጅሀድ ካሉ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ሁሉ ይሻላል፡፡

አብደላህ ኢብን ኡመር እንዳስተላልፈው

አንድ ሰው በጅሀድ ላይ ሊሳተፍ ፈልጎ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ይቀርባል፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) “ወላጆችህ በህይወት አሉን? ብለው ይጠይቁታል፡፡ “አዎን” ብሎ ይመልስላቸዋል፡፡ “ወላጆችህን በማስደሰትና በመታዘዝ ጅሀድ አድርግ” ብለውታል፡፡

ይህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) ባስተላለፈው ሌላ ሐዲስ ተረጋግጧል፡፡

የአላህን ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) “የአላህ ነብይ ሆይ! በአላህ ዘንድ እጅግ ተወዳጁ ተግባር ምንድነው?” ብዬ ጠየኳቸው፡፡ “ሶላትን በወቅቱ መስገድ” አሉኝ፡፡ “ከዛስ ቀጥሎ የአላህ መልእክተኛ?” እሳቸውም “ለወላጆችህ መልካም፣ ጥሩ፣ አክባሪ፣ ታዛዥና ተንከባካቢ መሆን” ብለው መለሱልኝ፡፡ “ከዚስ ቀጥሎ የአላህ መልእክተኛ?” “በአላህ

መንገድ ላይ መታገል” አሉኝ፡፡ (ቡኻሪ 56.25 እና መስለም /139)

አብደላ ቢን ዐምር ቢን አል-አስ (ረ.ዐ) ባስተላለፈው ሌላ ሐዲስ

“አንድ ሰው ወደ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ይመጣና ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከእርሶ ጋር ለመሰደድና የእርሱን ምንዳ ብቻ በመፈለግ በአላህ መንገድ ላይ እታገላለሁ› ይላቸዋል፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) ሰውየውን ይጠይቁታል፡፡ “ወላጆችህ በህይወት አሉን?” ሰውዬውም “አዎን የአላህ መልክተኛ ሆይ! ሁለቱም በህይወት አሉ” ብሎ ይመልስላቸዋል፡፡ እርሳቸውም “ከአላህ ምንዳ ትፈልጋለህን?” ብለው ይጠይቁታል፡፡ “አዎን” አላቸው፡፡ “እንግዳውስ ወደ ወላጆችህ ተመለስና ምርጥና መልካሙ ወዳጆቻችው ሁን!” ይሉታል፡፡ (ሙስሊም 2549)

በሌላ ትክክለኛ ሐዲስ ውስጥ ሙዓዊያህ አስ-ሱላሚ (ረ.ዐ) ያስተላለፈው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር እንዲህ ሰፍሯል፡፡

“በአላህ መንገድ ላይ ወደ ጅሀድ መሄድ እፈልጋለሁ” ይላቸዋል ሙዓዊያህ የአላህ መልእክተኛን (ሰ.ዐ.ወ)፡፡ እርሳቸውም “እናትህ በህይወት አለችን?” ሲሉ ይጠይቁታል፡፡ እርሱም “አዎን” ይላቸዋል፡፡ “ከእርሷ ጋር ሁን፤ ጀነት በእግሮቿ ስር ናትና” ይሉታል፡፡ (አህመድ 1557 እና ነሳኢ 3104፤ የተረጋገጠ)

እናቶች ከአባቶች ይበልጥ መልካምነት፣ አገልግሎት፣ መልካም እንክብካቤና ቀረቤታ ይገባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ልጆችን በማሳደግ ረገድ ያለውን ልፋት በቅፅበት ደረጃ ያስተናገዱት እነርሱ ናቸው፡፡ ቡኻሪና ሌሎች የሚከተውን አቡ ሁሬይራ (ረ.ዐ) ያስተላለፉትን ሀዲስ ዘግበውታል፡፡

አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይመጣና “የአላህ መልክተኛ ሆይ! የኔ መልካም ክብካቤ የሚገባው ማነው?” ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ የአላህ መልእክተኛም “እናትህ” ሲሉ ይመልሱለታል፡፡ ሰውየውም “ከእርሷስ ቀጥሎ?” ይላቸዋል፡፡ “እናትህ” ይሉታል፡፡ “ከእርሳስ ቀጥሎ?” ብሎ ደግሞ ይጠይቃቸዋል፡፡ እርሳቸውም “እናትህ” ይሉታል፡፡ ሰውየውም “ከእርሷስ ቀጥሎ?” ብሎ ለ4ኛ ጊዜ ሲጠይቃቸው እርሳቸው “አባትህ” ብለው ይመልሱለታል፡፡ (ቡኻሪ 5625 እና ሙስሊም 2548)

ይህ ሀዲስ እንደሚያመለክተው እናት ከልጅ በተያያዘ ማርገዟ፣ መውለዷ፣ ማጥባቷና ማሳደግ ከአባት ይበልጥ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንድታሳልፍ ስለሚያደርጋ ከአባት በ3እጅ የበለጠ መብት አላት፡፡

አላህ (ሱወ) በቅዱስ ቁርአኑ

“ሰውንም በወላጆቹ (በጎ እንዲያደርግ) በጥብቅ አዘዝነው፤ እናቱ ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው፤ ጡት መጣያውም በሁለት

ዓመት ውስጥ ነው፤ ለኔም ለወላጆችህም አመስግን በማለት (አዘዝነው)፤ መመለሻው ወደኔ ነው።" (31፡14)

በእስልምና አስተምህሮት እና መርህ ሁለቱም ወላጆች ሊከበሩ፣ ሊታዘዙና ልጆቻቸውን በአላህ ላይ እንዲያምፁ እስካለዘዙዋቸው ድረስ ትእዛዛቸው ሊከበር ግድ ይላል፡፡ በፈጣሪ ላይ አመጽ ትእዛዛቸው ወደጎን ተብሎ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ግን ምንም ሳይጓደልባቸው ይቀጥላሉ፡፡ ልጆች ወላጆቻቸውን በህይወት ጉዳዮቻቸው በሙሉ እንዲያገለግሏቸው፣ እንዲያግዙዋቸው፣ ሲቸገሩ እንዲደርሱላቸው ይጠበቃል፡፡

አላህ ሱወ በቅዱስ ቁርአኑ እንደተናገረው

"ለአንተ በርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር በኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም፣ አትታዘዛቸው፤ በቅርቢቱም ዓለም፣ በመልካም ስራ ተወዳጃቸው፤ ወደኔም የተመለሰን ሰው መንገድ ተከተል፤ ከዚያም መመለሻችሁ ወደኔ ነው፤ ትሰሩት የነበራችሁንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፤ (አልነው)።" (31፡15)

ወላጆች ከእስልምና ውጭ ያለ ሃይማኖት ቢከተሉ እንኳ መከበራቸው፣ ለነርሱ መታዘዝና በገንዘብ መረዳታቸው አንዳችም መጓደል ሳይደርስበት ይቀጥላል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ትእዛዛቸው የማይከበረው ልጆቻቸውን በአላህ ላይ እንዲያምጹ እስካልጠየቁ ድረስ ብቻ ነው፡፡

አሳማ ቢንት አቡ በከር (ረ.ዓ) ገጠመኟን እንዲህ ታካፍለናለች፡፡ “ጣዖት አምላኪዋ እናቴ ልትጠይቀኝ ትመጣለች፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ወ.ዐ) ጋር ሄድኩና ‹እናቴ ልትጠይቀኝ መጥታለች፡፡ በእስልምናም ተስባለች፤ ከእርሷ ጋር ያለኝን ግንኙነት ልቀጥል?› አልኳቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹አዎን በርግጥ ከእናትሽ ጋር ግንኙነትሽን ቀጥዪ› ብለውኛል፡፡”

ወላጆችን አለመታዘዝ፣ አለማክበርና መብቶቻቸውን አለማሟላት ትልቅ ሃጢያት ነው፡፡ የእዚህ ሃጢያት ቅጣት እስከመጪው ዓለም ድረስ አይቆይም፡፡ በአሁኑ ህይወታችን ይወራረዳል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ

“በሚቀጥለው ዓለም ከሚጠብቀው በላይ በዚህም ዓለም እንደ ጭቆናና ዝምድናን መቁረጥ ቅጣት የሚያመጣ የለም፡፡” (ቲሪሚዚ 2511 እና ኢብን ማጃህ 4211)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በተጨማሪ ሲናገሩ

“አላህ እናታችሁን አለመታዘዝ፣ (መስጠት የሚገባችሁን) ማቀብ ወይም (የማይገባችሁን) ከመጠበቅና ሴት ልጆቻችሁን መቅበር ከልክሏችኋል፡፡ አላህ የማይጠቅም ወሬን፣ (ምንም አይነት ፋይዳ የሌላቸውን) በርካታ ጥያቄዎችን መጠየቅና ሃብታችሁን ማባከን ይጠላል፡፡” (ቡኻሪ 5630)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለወላጆች መልካምንና ጥሩ መሆን ፀሎት (ዱዓእ) በአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በረጅም ሐዲሳቸው አሳይተዋል፡፡

“ከቀደምት ጊዜያት ሶስት ሰዎች ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ ቀኑ ሲመሽ ሌሊቱን ለማሳለፍ ከተራራረ ስር ካለ ዋሻ ውስጥ እንደገቡ ትልቅ ቋጥኝ ዋሻውን ይዘጋዋል፡፡ በገጠማቸው ሁኔታ ላይ ከተነጋገሩ በኋላ ከዚህ ችግር በዱዓእ ካልሆነ በስተቀር ሊወጡ እንደማይችሉ ይደመድማሉ፡፡ ‹በህይወታችን ውስጥ የሠራነው መልካምና የፅድቅ ሥራ እያስታወስን አላህ እንለምነው፡፡›

የመጀመሪያው ሰው ‹አላህ ሆይ! ሁለት እድሜያው የገፉ ወላጆች አሉኝ፡፡ ለእነርሱ የሚበላ ሳላቀርብ ለልጆቼ እና ለባለቤቴ ምግብ አላቀርብም፡፡ አንድ ቀን ለከብቶቼ የግጦሽ ሳር ፍለጋ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄድኩ፤ ስመለስ ዘግይቼ ነበር፡፡ እንደደረስኩ ሁለቱ ወላጆቼ ተኝተው አገኘኋቸው፡፡ ለወላጆቼ የሚሆን ወተት ከበጎች አለብኩኝ፡፡ ነገር ግን ከእንቅልፋቸው መቀስቀስ ስላልፈለኩ እስኪነሱ ድረስ ወተት ማሰሮውን ይዤ አጠገባቸው ቆሜ መጠባበቅ ያዝኩኝ፡፡ ለእነርሱ የሚበላ እስከምሰጣቸው ድረስ ለባለቤቴም ለልጆቼም አልሰጣቸውም ነበር፡፡ ሊነጋጋ ሲል በእንቅልፋቸው ተነሱ፡፡ በዚህ ጊዜ ልጆቼ በርሃብ እያለቀሱ ነበር፡፡ ወተቱን ሰጦኋቸው፡፡ አላህ ሆይ! ይህን የሰራሁት ለአንተ

መሆኑን ከመሰከርክልኝ እባክህ ከዚህ ወጥመድ አውጣን › አለ፡፡ ይሄኔ መግቢያውን የገጠመው ቋጥኝ ፈቀቅ አለ፡፡

ሁለተኛው ሰውም ‹አላህ ሆይ! ከአባቴ በኩል የሆነች፣ በምድር ላይ እንደርሷ ለኔ ተወዳጅ የለሌች የአጎቴ ልጅ ነበረች፡፡ ለእርሷ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም አልቀበልህም አለችኝ፡፡ በሆነ ወቅት ላይ በርሃብ ምክንያት ገንዘብ ችግር ውስጥ ገባች፡፡ እርዳታዬን ፈልጋ ወደኔ መጣች፡፡ ከእርሷ የምፈልገውን ከሰጠችኝ አንድ መቶ ዲናር ልስጥሽ አልኳት፡፡ ካለባት አንገብጋቢ ችግርና የገንዘብ ቀውስ በሃሳቤ ተስማማች፡፡ ከእርሷ ጋር ሀሳቤን ለመፈፀም ስንደረደር ‹የአጎቴ ልጅ ሆይ! አላህን ፍራ፤ በህጋዊ መንገድ ካልሆነ ድንግልናዬን አትውሰድ› አለችኝ፡፡ ይህን እንደሰማሁ ከአጠገቧ ተነሳሁ፣ ምንም እንኳ በእርሷ አምሮት በእጅጉ ብንገበገብም፡፡ የሰጠኋትንም ወርቅ አልተቀበልኳትም› አለ፡፡

ከዚያ እጆቹን ከፍ አድርጎ ‹አላህ ሆይ ያደረጉትን ያንተን ደስታ በመሻት እንደሆነ ከመሰከርክልኝ ካለንበት ጭንቀት አውጣን፣ ከዚህ እንድንወጣ ዋሻውን የደፈነብንን ቋጥኝ ክፈትልን› ብሎ ፀለየ፡፡ ቋጥኙ ትንሽ ከፈት ቢልም ሾልኮ ለመውጣት በቂ አልሆነም፡፡

ሶስተኛው ሰው አለ፡፡ ‹አላህ ሆይ! አንድ ቀን ሰራተኞችን ቀጥሬ ስራ አሰርቼ በቀኑ መጨረሻ ደሞዛቸውን ሰጠኋቸው፤ አንዱ ግን ሳይቀበል ይሄዳል፡፡ ገንዘቡን በምሠራው ስራ ውስጥ ጨርምሬ እሠራበት ጀመር፡፡ የተለየ የሂሳብ ማስታወሻ አዘጋጅቼ እመዘግብም ነበር፡፡ የዚህ ሰራተኛም ገንዘብ በዓመታት ውስጥ አደገ፡፡ ከብዙ ዓመታት በኋላ ይህ ሰራተኛ የሰራበትን ደምወዝ ለመቀበል ይመጣል፡፡ እኔም ወደ በርካታ የበጎች፣ ላሞች፣ ግመሎች እና አገልጋዮች አመለከትኩና ‹የምታየው በሙሉ ያንተ ነው፤ ያለብኝ ገንዘብ ይህ ነው› አልኩት፡፡ ‹ባክህ አትቀልድብኝ፤ ልውሰድ የመጣሁት የአንድ ቀን ደምወዜን ነው› አለኝ፡፡ እኔም ‹እየቀለድሁ አይደለም፣ ሁሉም ያንተ ነው› አልኩት፡፡›

ከዚያ እጆቹን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ ‹አላህ ሆይ! ሥራዬ ያንተን ደስታ ለማግኘት እንደሆነ መስክረህልኝ ከሆነ ካለንበት ወጥመድ አድነን› አለ፡፡ ይሄኔ ቋጥኙ ከዋሻው በር ይንከበለልና ሶስቱም ሰዎች ነጻ ይወጣሉ፡፡”

እንደ እስልምና አስተምህሮ ወላጆችን መንከባከብ፣ ለነርሱ በጎ መዋል፣ ማክበር በዚህ ዓለም ውስጥ ከሚደርስብን የሃጢያት ቀንበር ነጻ ያወጣናል፡፡

አብደላህ ኢብን ዑመር (ረ.ዐ) ባስተላለፉት ሐዲስ

“አንድ ሰው ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይመጣና ‹ነቢዩ ሆይ! ከፍተኛ ሃጢያት ሠርቻለሁ፣ ከእርሱ ልሰረይ እችላለሁ?› ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ ነቢዩም ‹እናትህ በህይወት አለችን?› ሲሉ ይጠይቁታል፡፡ ሰውየውም እንደሌለች ይነግራቸዋል፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ‹የእናትህ እህት በህይወት አለች?› ይሉታል፡፡ ሰውየውም በህይወት እንዳለች ይመልስላቸዋል፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ‹ለርሷ መልካምና ጥሩ ሁን› አሉት፡፡” (ቲርሚዚ 1904 እና ኢብን ሂባን 435፤ የተረጋገጠ)

ይህ ሐዲስ አክስት ያላትን መብት ይጠቁማል፡፡ በእስልምና ህግ መሰረት በተወሰነ መልኩ እንደ እናት ክብር አላት፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉት “የእናት እህት እንደ እናት ተመሳሳይ ደረጃ አላት፡፡” (ቡኻሪ 2552)

እነዚህ ሰፊ መመሪያዎች ወላጆች በጥቅሉ፣ እናት በተለየ ያላትን ዋና ዋና መብቶች ያሳያሉ፡፡ በእስልምና አስተምህሮት እናቶች ያላቸውን ልዩ ክብር ያስረዳሉ፡፡

## ሴቶች እንደ ዘመድና ጎረቤት

በእስልምና ህግ ለወንዱ የጸደቀለት መብትና እንዲከበር የተረቀቁት ህግጋት በተመሳሳይ መልኩ ለሴቷም ይሠራሉ፡፡

የአጠቃላይ የህዝብ ደህንነትና አንዱ ከሌላው የመተባበር መንፈሥ ማዳበር የእስልምና የማህበራዊ ስርዓት መለያ ምልክት ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደሉት

"አማኞች አንዳቸው ለሌላው ባላቸው መልካምነት፣ መተዛዘንና መረዳዳት እንደ አንድ ሰውነት ናቸው፡፡ አንደኛው የሰውነት ክፍላችን ሲታመም አጠቃላይ ሰውነታችን በንቃትና ትኩሳት ምላሽ ይሠጣል፡፡" (ሙስሊም 2586)

በተጨማሪም ሲናገሩ

"አማኞች አንዳቸው ለሌላቸው በመረዳዳት እንደ ጥብቅ ህንጻ ናቸው" ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ 467 እና ሙስሊም 2585)

ሴት ልጅ አክስት፣ የአጎት ወይም የአክስት ልጅ ብትሆን ወይም በየትኛውም ርቀት ላይ የምትገኝ ዘመድ ብትሆን በአላህ (ሱ.ወ) መልካም፣ ጥሩና ደጋፊ ሁንላቸው ትእዛዝ ጥላ ውስጥ ትሆናለች፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን ውስጥ እንደሚናገረው

"ብትሸሾሙም በምድር ላይ ማበላሸትን ዝምድናችሁንም መቁረጥን ከጀላችሁን?" (47፡22)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ "ዝምድናን የቆረጠ ጀነት አይገባም፡፡" (ሙስሊም 2556)

በሌላ ንግግራቸውም

“ሰደቃ ለድሃ ሰደቃ ነው፡፡ (ለድሃ) ዘመድ ግን ሰደቃና ዝምድና መቀጠል ነው” ብለዋል፡፡ (ቲርሚዚይ 658 እና ኢብን ማጃህ 1849፤ የተገጋገጠ)

አንዲት ጎረቤት ሴት ሙስሊም ከሆነች ሁለት መብቶች ይገቧታል- የእስልምና እና የጎረቤት፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአኑ እንዲህ ይላል

“አላህን ተገዙ፤ በርሱም ምንንም አታጋሩ በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፣ በየቲሞች፣ በምስኪኖችም፣ በቅርብ ጎረቤትም፣ በጎን ባልደረባም፣ በመንገደኛም፣ እጆቻችሁም ንብረት ባደረጓቸው (ባሮች)፣ መልካምን (ሥሩ)፤ አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድም።” (4፡36)

እስልምና ሙስሊሞችን ለጎረቤቶቻቸው በሙሉ መልካም እንዲሆኑ ያስገድዳል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ..ወ) ሲናገሩ “ጎረቤት ህጋዊ ወራሽ ነው ብዬ እስካስብ ድረስ ጅብሪል ስለጎረቤት አስጠነቀቀኝ፡፡” (ቡኻሪ 5668)

በተጨማሪም ሲያስጠነቀቁ

“በአላህ እርሱ አማኝ አይደለም፤ በአላህ እርሱ አማኝ አይደለም፤ በአላህ እርሱ አማኝ አይደለም!” አሉ፡፡ አጠገባቸው የነበሩት “ማነው እርሱ?” ሲሉ የአላህ መልእክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ይጠይቋቸዋል፡፡ እርሳቸውም “ጎረቤቱ ከእርሱ ጉዳት ያልተጠበቀ” ብለው ይመልሳሉ፡፡ (ቡኻሪ 5670)

አስፋሃኒ በሂልያቱል-አውሊያ ጠልሃ የተናገረውን እንደሚከተለው ዘግቦታል፡፡

“በአንደኛው ሌሊት ዑመር ኢብን ኸጣብ (ረ.ዐ) ወደ ቤቱ ሲሄድ በለሊት ምን እንደሚሠራ ለማየት ተከተልኩት፡፡ ወደ አንድ ቤት ሲገባ አየሁት፤ ከትንሽ ቆይታ በኋላ መልሶ ወጥቶ ሌላ ቤት ይገባል፡፡ በጠዋት ማን እንደሚኖርበት ለማወቅ ወደ መጀመሪያው ቤት ገባሁ፡፡ በጣም የደነቀኝ ነገር በቤት ውስጥ አንዲት አሮጊት፣ አይነ ስውርና አካል ጉዳተኛ አገኘሁ፡፡ “ማታ መጥቶ የነበረው ሰው ከአንቺ ምንድነው የሚፈልገው” ስል ጠየቅኋት፡፡ “ይህ ሰው ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ የሚንከባከበኝ ነው፡፡ የሚያስፈልገኝን ያሟላልኛል፤ ይረዳኛል፤ ይደግፈኛል” ብላ መለሰችልኝ፡፡ እኔም ለራሴ “ለምን ይሆን የዑመርን ተግባር የምመረምረው አልኩኝ፡፡”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲነገሩ

“ባለቤቶቻቸው የሞቱባቸውና ድሆችን የሚንከባከብ ሰው በአላህ መንገድ ላይ እንደሚታገል ነው፡፡” ዘጋቢው “ሌሊቱን ያለድካም

እየሰገደ እንደሚያድርና ቀኑን ሙሉ ሲፆም እንደዋለ ነው” የሚለውንም ጨምረዋል መሰለኝ ብሏል፡፡” (ቡኻሪ 5038 እና ሙስሊም 2982)

እስካሁን የተነጋገርንባቸው ነጥቦች እንደ እስልምና አስተምህሮ ሃይማኖት ለሴቶች የሰጠው መብት እና በጥቅሉ የሚያሳዩ፣ ለሴቷ ሊሠጡ የሚገባውን ክብር፣ ማዕረግ፣ ክብክባኔ እና የጋራ ልዩ ገጽታዎችም ናቸው፡፡ ለሴቶች የዚህን ያህል ክብርና ማዕረግ በሰው ልጆች ታሪክ ተከብሮላቸው እንደማያውቅ እናምናለን፡፡ የእስልምና ህግ ሴት በየትኛውም የህይወት ዕድገቷ ላይ ሊደርስ የሚችልባትን ወንጀል ፈቃጅ አይደለም፡፡

## ሴቶች በእስልምና እና የተለመዱ ስሁት ሃሳቦች እና ማስተካከያ

### የክብር ግድያ (Honor Killing)

በተወሰኑ ኋላ ቀርና ጎሳዊ ልምድ መሰረት ለሴቷ አግባብ ባልሆነ ድርጊት (ዝሙት) ክብሯን ካዋረደች፣ ማረጋገጫ ባይኖረው እንኳ ወንዱ ክብሩን ለመጠበቅ ሲል ሴቷን እንዲገድላት ይፈቀድለታል፡፡ይሉኝታ ቢስ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ይህን ልምድ

እስካሁን ድረስ እንዲቀጥል ስላደረጉ ሚዲያዎች እያራገቡት ይገኛል፡፡

ለዚህ መልሱ ቀላል ነው፡፡ ሲጀምር ሰዎች ህጉን እንዳሻቸው ተርጉመው ፍርድ መውሰድ የለባቸውም፡፡ እስልምና በተለይ ያልተረጋገጠ የዝሙት ውንጀላ ላይ ያለው እጅግ ጥብቅ አቋም ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ተግባሩ ከሃይማኖቱ ህግ አንጻር በተጻራሪ የቆመ ነው፡፡ እንደውም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አጣርቶ በተቃራኒው አሳማኝ ምክንያት ካገኘ ገዳዩን በወንጀል ይቀጣዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ተግባር በሚፈፀምባቸው ሃገራት ያሉ ፖለቲከኞች ለፖለቲካ ጥቅማቸው ሲሉ ከጎሳ እና ሌሎች መሪዎች ጋር ስለሚያሻቅብጡ ይህ ኢፍትሃዊ ልማድ እስካሁን ሊቀጥል ችሏል፡፡ እስላማዊ ህግ ቢዘረጋ ኖሮ ፍትህ ሰፍኖ የብቀላ ጥማትን ባከሰመ ነበር፡፡

**ውርስ**

አላህ (ሱ.ወ) በቅዱስ ቁረኣን ውስጥ እንዳስቀመጠው

“አላህ በልጆቻችሁ (ውርስ በሚከተለው)፣ ያዛችኋል፣ ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ብጤ አለው፤ (ሁለት ወይም) ከሁለት በላይም የሆኑ ሴቶች ብቻ ቢሆኑ፣ ለነሱ (ሟቹ ) ከተወው ረጀት ከሦስት ሁለት እጁ አላቸው። አንዲትም ብትሆን ለርሷ ግማሹ አላት። ለአባትና ለእናቱም፣ ለርሱ ልጅ እንዳለው ከሁለቱ ለያንዳንዱ ከስድስት አንድ አላቸው። ለርሱም ልጅ ባይኖረውና

ወላጆቹ ቢወርሱት፣ ለእናቱ ሢሶው አላት። ለርሱም ወንድሞችና እህቶች ቢኖሩት ለእናቱ ከስድስት አንድ አላት፣ (ይህም የተባለው) በርሷ ከተናዘዘባት ኑዛዜ ወይንም ከዕዳ በሁዋላ ነው። አባቶቻችሁና ልጆቻችሁ፣ ለናንተ በመጥቀም ማንኛቸው ይበልጥ ቅርብ እንደሆኑ አታውቁም። (ይኸም) ከአላህ የተደነገገ ነው፤ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና።" (4፡11)

እስልምናን ባግባቡ ያልተረዱ ሰዎች ሃይማኖቱ በውርስ ጉዳይ ሴትን ይበድላል የሚል ክስ ያቀርባሉ፡፡ ሴትና ወንዱ ከተመሳሳይ ወላጅ ተወልደው ሴቷ የወንዱን ግማሽ መውረሷ ኢፍትሃዊነት ነው የሚል ሃሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ አላህ ሱ.ወ ስለሴቶች ውርስ በቅዱስ ቁርአንና በሱና ያስቀመጠውን ዝርዝር ሃሳብ ለመረመረ የክሱንና የሃሳቡን ስህተት ይረዳል፡፡

ጥበበኛው እንደሚለው

"ለወንዶች፣ ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተዉት (ንብረት) ፋንታ አላቸው። ለሴቶች፣ም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተዉት ከርሱ ካነሰው ወይንም ከበዛው፣ ፋንታ አላቸው። የተወሰነ ድርሻ (ተደርጓል)።" (4፡ 7)

አላህ ሱ.ወ ለሴቷ ሶስት አይነት መብቶች አስቀምጧል፡፡

1. ሴቷ ከወንዱ ጋር እኩል ትወርሳለች

2. አንዲት ሴት ከወንድ እኩል ወይም ያነሰ ልትወርስ ትችላለች

3. አንዲት ሴት የወንዱን ግማሽ ትወርሳለች፡፡

ይህ ማለት የሴቷ ዝቅተኛ ድርሻ ግማሽ ነው፡፡ ወንዱ ባለበት ሴቶች እንደ እህት፣ ሚስት ወይም እናት ምንም ዓይነት ገንዘብ ለቤተሰባቸው የማዋጣት ሃላፊነት በሌለባቸው ሁነት ይህ ፍትሃዊ አይደለም አይባልም፡፡

ከሌሎች ህብረተሰቦች፣ የእስልምና ህገ ሥርዓት በሰዎች ግንኙነት ህብር ለመፍጠር በሰዎች ጉዳዮች ላይ፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ ህግጋትና ደንቦች አሉ፡፡ ለምሳሌ ሰዎች ገንዘባቸውን እንዴት ማግኘት እንዳለባቸው፣ በምን መልኩ መጠቀም እንዳለባቸውና ከሞቱም በኋላ በምን አይነት መንገድ ማስተላለፍ እንዳለባቸው መመሪያዎች ተቀምጠዋል፡፡ ምንም እንኳ በሌሎች ህብረተሰቦች ውስጥ ወንድ ገንዘቡን በምን አይነት መልኩ መጠቀም እንዳለበት ገደቦች ባይኖሩም በእስልምና ህግ ግን እንዲህ አይነት ነገር የለም፡፡ ከሃብቱ ለ1/3ኛውን ብቻ ነው ለፈለገው ማውረስ የሚችለው፤ የተቀረው የሚከፋፈለው በቅዱስ ቁርአን በተቀመጠው መሠረት ነው፡፡

በታዋቂው ሐዲስ ሰሃባው ሰዓድ ኢብን አቢ ወቃስ (ረ.ዐ) ታሞ ከሃብቱ አብዛኛውን ወይም ግማሹን ምጽዋት ሊሰጥ ይፈልጋል፡፡ ሃብታም ነው፤ አንደት ሴት ልጅ ብቻ ናት ያለችው፡፡ የአላህ

መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ግን ክልክለውት 1/3ኛውን ብቻ ፈቅደውለታል፡፡

“አንድ ሶስተኛውን፤ አንድ ሶስተኛው ብዙ ነው፡፡ ወራሾችህን ችግር ውስጥ ከተህ የሰው ፊት እንዲያዩ ከምታደርጋቸው ሃብታም ብታደርጋቸው ይሻላል፡፡ የአላህን ፊት ፈልገህ ምንም ነገር አታወጣም፣ ለምታወጣው ነገር ምንዳ የማታገኝበት ቢሆን እንጂ፣ ለባለቤትህ የምታጎርሳት ጉርሻ ቢሆን እንኳን፡፡” (ቡኻሪ 2591 እና ሙስሊም 1628)

በዚህ ጉዳይ ላይ መስተዋል ያለበት ነጥብ በአብዛኛው ስልጣኔ የሰዎች ውርስ በሃያላን ግለሰቦች ስሜት ላይ የተነጣጠለ መሆኑን ነው፡፡ የቱን ያህል ፍትህ የጎደለ ቢሆን አንዱ እንዳሻው ይሰጣል፣ ይነፍጋል፡፡ በተጨማሪም በነዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ወንዱ በገንዘብ ጉዳይ የሚያስገድደው ምንም አይነት አስገዳጅ ህግ የላቸውም፡፡ በመሆኑ ሴቶችን ከነርሱ ነጥለዋቸዋል፡፡

ከሌላ በኩል እንደ እስልምና ሴቷ አግብታ እስክትወጣ ድረስ የትኛውንም አይነት የገንዘብ ፍላጎቷን ማሟላት ያለበት ወንድ ነው፡፡ ልክ ስታገባ ሃላፊነቱ ወደ ባሏ ይዘዋወራል፡፡ ባሏ ከሞተ ደግሞ ወንድ ወይም ሌላ ወንድ ዘመድ ሃላፊነቱን ይቀበላል፡፡

ስለዚህ ሴቶች ከወንድ እኩል የገንዘብ ግዴታ እና ሃላፊነት በሌለባቸው ሁኔታ እኩል ውርስ መብት ይቸራቸው ብሎ

መጠቆም በምንም መልኩ ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም፡፡ ካለበት የገንዘብ ሃላፊነትና ግዴታ ከአባት የሚተላለፍ ውርስ ከሴቷ በተሻለ ለወንዱ ድርሻ መኖሩ ፍትሃዊ ነው፡፡

Arab civilization በሚለው መፅሐፍ ጉስታቭ ለቦን እንደፃፈው *“በቅዱስ ቁርአን የተወሰነው የውርስ መርህ ታላቅ ፍትህ እና ሚዛናዊነት አለው፡፡ በጠቀስኳቸው የቁርአን አንቀፆች ቅዱስ ቁርአንን የሚያነብ ሰው በውርስ ረገድ የፍትህና የሚዛናዊነት ፅንሰ ሃሳብ መገንዘብ ይችላል፡፡ ጥቅል ህጎች እና ደንቦች በተመለከተ ከነዚህ አንቀፆች የሚገኘውን ከፍተኛ ብቃት መጠቆም አለብኝ፡፡ የእንግሊዝን፣ የፈረንሳይን እና የእስልምናን የውርስ ህግ አነጻፅሬ እስልምና የእኛ ህጋጋት የሌሎላቸው የውርስ መብት እንዳረጋገጠ ተረድቻለሁ፡፡ ምንም እንኳ ምዕራብያውያን ሚስቶች በሙስሊም ወንዶች ተገቢ ባልሆነ መልኩ ይያዛሉ ቢሉም፡፡”*

## የሴቶች የመስራት መብት

እስልምና መብቷና ክብሯ ማይነኩ ስራንም እንድትሰራ ይፈቅዳል፡፡ እስልምና ሴቷ ንብረቷንና ገንዘቧን ትርፋማ በሆነ መንገድ ስራ እንድትሰራበት ያበረታታል፡፡ የስራ ግንኙነቶች

በሙሉ ግን ህጋዊ አግባብ ባለው በሆነ መልኩ ግዴታ ይጥላል፡፡ ሌላው ሌሎች ግዴታዎቿን በማይበድል መልኩ መሆን አለበት፡፡